# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

82ኛ ዓመት ቁጥር 285 ሰኔ 15 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









ፎቶ - ዳኜ አበራ

ዶክተር ሊያ ታደሰ

ዶክተር ግርማ አመንቴ

# የምግብ ሥርዓትና ሥነ-ምግብ ትራንስፎርሜሽን

## አጀንዳን ለማሳካት አገራዊ አቅሞችን አሟጦ መጠቀም ያስፈልጋል

### - የሚኒስትሮች ስቲሪንግ ኮሚቴ የምስረታ ጉባኤውን አካሂዷል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን የምግብ ሥርዓት እና ሥነ-ምግብ ትራንስፎርሜሽን አጀንዳን እውን ለማድረግ አገራዊ አቅሞችን ሁሉ አሟጦ መጠቀም እንደሚገባ የኢትዮጵያ የምግብ ሥርዓትና ሥነ-ምግብ የሚኒስትሮች ስቲሪንግ ኮሚቴ ገለጸ፡፡ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶክተር) የተቋቋመው የኢትዮጵያ የምግብ ሥርዓትና ሥነምግብ የሚኒስትሮች ስቲሪንግ ኮሚቴ የምስረታ ጉባኤውን ትናንት አካሂዷል፡፡

የኢትዮጵያ የምግብ ሥርዓትና ሥነ-ምግብ የሚኒስትሮች ስቲሪንግ ኮሚቴውን ከሚያስተባብሩት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች አንዱ የሆነው የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰ በወቅቱ እንደገለጹት፤ እንደ አገር የምግብ ሥርዓትና የሥነምግብ ስትራቴጂ ተቀርጾ ላለፉት 10 ዓመታት ሢሠራ ቆይቷል። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ በ2030 እ.አ.አ ልታሳካው ያቀደችውን የምግብ ሥርዓት እና ሥነ-ምግብ ትራንስፎርሜሽን አጀንዳን እውን ለማድረግ አገራዊ አቅሞችን አስተባብሮ መጠቀም ይፈልጋል፡፡

የምግብ ሥርዓትና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል











አቶ ሠለሞን ደስታ

# ብሔራዊ ባንክ

## ለአምስት የውጭ አገር ባንኮች ፈቃድ ሊሰጥ ነው

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**

አዲስ አበባ፡- አምስት የውጭ አገር ባንኮች ኢትዮጵያ ውስጥ ገብተው አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችላቸው ፈቃድ እንደሚሰጣቸው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አስታወቀ፡፡ አገር በቀል ባንኮች ከወዲሁ ከፍተኛ ዝግጅት ማድረግ እና ቀድሞ የነበራቸውን ስትራቴጂ መከለስ እንዳለባቸውም አሳሰቧል፡፡

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ የገንዘብ ተቋማት ዘርፍ ምክትል ገዥ አቶ ሠለሞን ደስታ ከኢፕድ ጋር ባደረጉት ቆይታ፤ የአገር ውስጥ የፋይናንስ ተቋማትን ከማጠናከር ጎን ለጎንም የውጭ ባንኮችን ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት እየተሰራ ነው፡፡

«ሥራውን አሁን እያጠናቀቅን ነው፡፡ አዋጁን የመከለስ

ብሔራዊ ባንክ ... ወደ ገጽ 12 ዞሯል






# ጠለፋ - በሕግ እይታ

**ሄለን ወንድምነው**

ሴቶች ላይ ለሚደርሱ ዘርፈ ብዙ ጥቃቶች የተሳሳተ የባህል አመለካከት፣ የዕውቀት ማነስ፣ የህግ ክፍተት እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች እንደመንስዔ ይጠቀሳሉ፡፡ ከሚደርሱት ጥቃቶች መካከል አንዱ የጠለፋ ወንጀል ነው፡፡ የጠለፋ ወንጀል በተለያዩ የአፍሪካ እና የእስያ አገራት እንደሚታይ ጥናቶች የሚመላከቱ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ አንዳንድ አካባቢዎች አዲስ በሚመስል መልኩ እየተፈጸመ ይገኛል፡፡

ለዚህም ማሳያ የሚሆኑት በማህበራዊ የትስስር ገፆች ወደህዝብ ጆሮ የደረሱት በሲዳማ ክልል ሀዋሳ

ጠለፋ- ... ወደ ገጽ 12 ዞሯል



## “ለዜጎች የሚደረግ እርዳታን የማቆም ውሳኔ ፖለቲካዊ አንድምታ ያለበት ነው”

- አምባሳደር ጥሩነህ ዜና
  የቀድሞ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽነር

ገጽ 4




# የኢትዮጵያ አየር መንገድ

## የናይጄሪያ ብሔራዊ አየር መንገድን ወደ ሥራ ለማስገባት መዘጋጀቱን አስታወቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ የናይጄሪያ ብሔራዊ አየር መንገድን በጥቂት ወራት ውስጥ በማቋቋም ወደ ሥራ ለማስገባት የሚያስችሉ የዝግጅት ሥራዎች እየተጠናቀቁ መሆኑን አስታወቀ፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በ49 በመቶ ድርሻ የናይጀሪያ ብሔራዊ አየር መንገድን ለማቋቋም ስምምነት በመውሰድ ወደ ሥራ መግባቱ ይታወሳል፡፡

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ ዋና ሥራ አስፈጻሚ መስፍን ጣሰው ለኢዜአ እንደተናገሩት፤ አየር መንገዱ በአህጉሪቷ አቪዬሽን ዘርፍ ግዙፍና ትርፋማ ሆኖ ቀጥሏል፡ ፡

በዚህም አየር መንገዱ የተለያዩ የአፍሪካ አገራት አየር መንገዶችን ሙሉ በሙሉና በከፊል የማስተዳደር ሥራውን እውን እያደረገ ይገኛል ብለዋል።

የናይጀሪያ ብሔራዊ አየር መንገድን ለማቋቋም ስምምነት ላይ መደረሱን ተከትሎም የተለያዩ የዝግጅት ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ተናግረዋል።

በአሁኑ ወቅትም አየር መንገዱን ለማቋቋም ከናይጀሪያ መንግሥትና ባለድርሻ ከሆኑ የናይጀሪያ ባለሀብቶች ጋር ሰፊ




ውይይት በማድረግ ስምምነቶች መፈረማቸውን ገልጸዋል።

እንዲሁም ከናይጀሪያ ሲቪል አቪዬሽን ባለስልጣን "የኤር ኦፕሬተር ሰርተፊኬት" ለመቀበል ሂደቶች መጀመራቸውን ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ኮሚቴ በማቋቋም አጠቃላይ የዝግጅት ሥራዎችን በትኩረት እያከናወነ መሆኑንም ነው ያብራሩት፡፡

በዚህም እስከ መጪው ጥቅምት ወር የናይጄሪያ ብሔራዊ አየር መንገድ ተቋቁሞ በረራ እንዲጀምር እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

"ዝግጅቱን አሁን እያካሄድን ያለነው በመስከረም ወይም ጥቅምት ላይ አየር መንገዱ በረራ እንዲጀምር በሚያስችል ሂደት ውስጥ ነው ያለነውና በጥብቅ እየተከታተልን ነው" ብለዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከቶጎ "አስካይ አየር መንገድ"፤ "ከማላዊ አየር መንገድ " እንዲሁም "ከዛምቢያ ኤር ወይስ" ጋር በጋራ እየሰራ ይገኛል፡፡

በተጨማሪም አየር መገዱ ከኮንጎ አየር መንገድ ጋር የነበረውን ሽርክና መልሶ ለመጀመር ከኮንጎ መንግስት ጋር ንግግር እያደረገ መሆኑ ተገልጿል።

የናይጄሪያ ብሔራዊ አየር መንገድ ወደ ሥራ ሲገባም የኢትዮጵያ አየር መንገድ አፍሪካን በአቬየሽን ዘርፍ ለማስተሳሰር በሚያከናውነው ስራ ላይ ተጨማሪ አቅም ይፈጥራል፡፡

የናይጄሪያ ብሔራዊ አየር መንገድ ሲቋቋም የኢትዮጵያ አየር መንገድ 49 በመቶ ድርሻ የሚይዝ ሲሆን፤ 5 በመቶ የናይጄሪያ መንግሥት እንዲሁም የተቀረውን 46 በመቶ ደግሞ ሶስት የናይጄሪያ ባለሀብቶች እንደሚጋሩት ተጠቁሟል።




# ባንኩ ከወለድ ነጻ በሆነው አገልግሎቱ ከ90 ቢሊዮን ብር በላይ አሰባስቧል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ ፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከወለድ ነጻ በሆነው አገልግሎቱ ከ90 ቢሊዮን ብር በላይ ማሰባሰቡን አስታወቀ፡፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለበይክ ተቀማጭ ሂሳብን" ሀጅ ለሁሉም" በሚል መሪ ቃል የሦስተኛ ዙር የንቅናቄ ማስጀመሪያ መርሀ ግብር አካሂዷል፡፡

በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወለድ ነጻ አገልግሎት ምክትል ዳይሬክተር አቶ ኑሪ ሁሴን እንደገለጹት፤ ባንኩ ባለፉት 10 ዓመታት የሙስሊሙን ህብረተሰብ ፍላጎት መሰረት ያደረጉና የሸሪአ መርሆችን የተከተሉ የተለያዩ የባንክ አገልግሎቶችን በማቅረብ ላይ ይገኛል፡፡

በዚህም በወለድ ነጻ አገልግሎቱ ከ6 ሚሊዮን ደንበኞች እስከ 90 ቢሊዮን ተቀማጭ ማሰባሰብ የቻለ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥም እስከ 20 ቢሊዮን ብር ለደንበኞች እያቀረበ ይገኛል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ኑሪ ገለጻ ባንኩ ከአንድ ሺ 915 በላይ የሚሆኑ ቅርንጫፎች ያሉት ሲሆን፤ ከነዚህ ውስጥም 147ቱ ሙሉ በሙሉ ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎት የሚሰጡ ቅርንጫፎች ናቸው።

ከወለድ ነጻ የባንክ አገልግሎቶች ለእስልምና እምነት ተከታዮች የእምነት ግዴታቸውን እንዲወጡ የሚረዳ ነው ያሉት አቶ ኑሪ፤ ለበይክ ተቀማጭ ሂሳብ በአደራ ተቀማጭ በሆነው ወዲዓህ እና ትርፍ አጋሪ በሆነው ሙደራባህ ተዘጋጅቶ በዋነኛነት አማኞች የሐጅ ሥነ-ሥርዓትን በረጅም ጊዜ ቁጠባ ለመፈጸም እንዲችሉ የተመቻቸ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም የዑምራ ሥነ-ሥርዓትን ለመፈጸም የሚፈልጉ ደንበኞች ይህንኑ ሂሳብ በመጠቀም መቆጠብ ይችላሉ ብለዋል፡፡

ባንኩ የለበይክ የቁጠባ ሂሳብ በአሁኑ ጊዜ የተቀማጭ ሒሳቡ 80 ሺ 813 ደንበኞችን ያፈራ ሲሆን 773 ሚሊዮን ብር በላይም በዚሁ ሒሳብ መቆጠብ ችለዋል።

አቶ ኑሪ አያይዘውም በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተቀማጭ መጠን ከ1 ትሪሊዮን ብር በላይ የሆነ ሲሆን፤ የሀብት መጠኑ 1ነጥብ 3 ትሪሊዮን ብር መድረሱን ገልጸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የቅርንጫፍ ስርጭቱን ከ1915 በላይ ሲያደርስ የደንበኞች ቁጥርም 40 ሚሊዮን በላይ በማድረስ፣ ከሰማኒያ ሺ በላይ ሠራተኞችን በቋሚነት እና በኮንትራት በመቅጠር ለብዙዎች የስራ እድል ፈጥሯል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ኑሪ ገለጻ፤ ባንኩ በጅቡቲ እና በደቡብ ሱዳን ቅርንጫፍ በመክፈት ቀጣናዊ እና ዓለም አቀፋዊ የኢኮኖሚ ትስስር ለመፍጠር ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል።

# የተሰጣቸው ጊዜ አነስተኛ ቢሆንም

## ለመውጫ ፈተና እየተዘጋጁ መሆኑን ተማሪዎች ገለጹ

**ዳግማዊት አበበ**




አዲስ አበባ፡- በ2015 ለሚሰጠው አገር አቀፍ የመውጫ ፈተና በተጣበበ ጊዜም ቢሆን ዝግጅት እያደረግን ነው ሲሉ ተመራቂ ተማሪዎች ተናገሩ:: የዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተናው በአገር አቀፍ ደረጃ ከሐምሌ ሦስት እስከ ሐምሌ ስምንት ቀን 2015ዓ.ም እንደሚሰጥ ታውቋል::

በደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነት እና ተግባቦት ትምህርት ዘርፍ የአራተኛ ዓመት ተማሪ ሂሩት ግዛቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጸችው፤ ለ2015 የመውጫ ፈተና በእጃችን ላይ ያሉ ግብዓቶችን እንዲሁም በቤተ መጽሐፍት የምናገኛቸውን መጽሐፍቶች በማንበብ ላይ እንገኛለን::

መምህራንም ከዚህ በፊት ተምረን ያለፍናቸውን ኮርሶች ድጋሚ በማስተማር እያገዙን ይገኛሉ ያለችው ተማሪ ሂሩት፤ በተጨማሪም ተማሪዎች እርስ በርሳችን በመተጋገዝ ፈተናውን ለማለፍ ዝግጅት እያደረግን እንገኛለን ብላለች::

ነገር ግን የመጨረሻ ዓመት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ለመውጫ ፈተና የምናደርገው ዝግጅት ከባድ ሆኖብናል ያለችው ተማሪ ሂሩት፤ ዝግጅቱን የምናደርገው ከጥናታዊ ጽሑፍ በተረፈን ጊዜ ነው ብላለች::

እንደ ተማሪ ሂሩት ገለጻ፤ ሌሎች መደበኛ የቤት ሥራዎችን ከመውጫ ፈተናው ጋር አብሮ ማስኬድ ከባድ ነው:: ዩኒቨርሲቲውም የመውጫ ፈተና ትፈተናላችሁ ብሎ ለተማሪው ያስቀረለት ምንም አይነት የቤት ሥራ የለም::

ተማሪው ከስነልቦና አንጻር ለመውጫ ፈተናው አልተዘጋጀም ማለት ይቻላል ያለችው ተማሪዋ፤ መዉጫ ፈተናውን ብንወድቅ አንመረቅም የሚለው ተማሪውን በሙሉ ልብ እንዳይዘጋጅ አድርጎታል ብላለች::

በወልዲያ ዩኒቨርሲቲ አራተኛ ዓመት የፖለቲካል ሳይንስና ዓለምአቀፍ ግንኙነት ተማሪ ሲፈልግ በለጠ በበኩሏ፤ ለመውጫ ፈተና በምንወስዳቸው 15 የትምህርት አይነቶች ላይ ዝግጅት እያደረግን እንገኛለን:: ነገር ግን ተመራቂ ተማሪ እንደመሆናችን ከጊዜ አንጻር በጣም የተጨናነቅንበት ወቅት ነው ብላለች::

ሆኖም የመውጫ ፈተና ስለማይቀርና የእኛ የአራትና የአምስት ዓመት ልፋታችን መና እንዳይቀር የአቅማችንን ዝግጅት እያደረግን እንገኛለን ስትል አክላለች::

ተማሪው ወደ ዩኒቨርሲቲ ሲገባ መውጫ ፈተና ይኖራል የሚል ግንዛቤው ስላልነበረው በስነልቦና ረገድ አልተዘጋጀም ስትልም ገልጻለች ተማሪ ሲፈልግ::

ሌላኛው የወልዲያ ዩኒቨርሲቲ አራተኛ ዓመት የህብረተሰብ ጥናት (ሶሾሎጂ) ተማሪ የሆነው ሰለሞን ሙላት እንደገለጸው፤ በዩኒቨርሲቲው አብዛኛው ተማሪ የመመረቂያ ጽሑፍ እና የማጠናቀቂያ ፈተና ላይ ነው ትኩረት አድርጎ እየሰራ ያለው:: ለመውጫ ፈተና እየተዘጋጀ ያለው ጥቂት ተማሪ ነው:: እነዛ ጥቂት ተማሪዎችም የማጠናቀቂያ ፈተና አስቀድመው በመጨረሳቸው ነው::

ለመውጫ ፈተናው ዩኒቨርሲቲው ትኩረት አልሰጠውም ያለው ተማሪ ሰለሞን፤ አስተማሪዎችም ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ጋር ሲነጻጸር የሚያደርጉልን እገዛ በጣም አናሳ ነው ብሏል::

# ስምምነቱ ጾታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ዜጎች በዘላቂነት እንዲያገግሙ ይረዳል

**ማህሌት ብዙነህ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- ሚኒስቴሩ ከዩኒሴፍ እና ከጂፒጎ ጋር ያደረገው የፕሮጀክት ስምምነት በሥርዓተ ፆታ ጥቃት ተጎጂ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን በመደገፍ ከደረሰባቸው ችግር በዘላቂነት እንዲያገግሙ የሚያስችል መሆኑን የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር በግጭት የተጎዱ የሥርዓተ ፆታ ጥቃት ተጎጂ የሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎችን ለመደገፍ የሚያስችል የሥራ ውል ስምምነት ከዩኒሴፍ እና ከጂፒጎ ጋር በትናንትናው እለት ተፈራረመ፡፡

የሴቶች እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ ስምምነቱ በኢትዮጵያ በነበሩ የእርስ በእርስ ግጭቶችና ጦርነቶች ምክንያት ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸውን ሴቶች፣ ህጻናት እና ወጣቶችን ችግር በሚቀርፍ ጉዳይ ላይ ትኩረት ይደረጋል፡፡

ስምምነቱ ለሁለት አመታት የሚቆይ ሲሆን፤ በዓለም ባንክ በተደረገ የ70 ሚሊዮን ዶላር የገንዘብ ድጋፍ የሚተገበር ፕሮጀክት አካል ነው ያሉት ዶክተር ኤርጎጌ፤ አጠቃላይም ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል ብለዋል፡፡

እነዚህም በጦርነቱና በግጭቶች የወደሙና የተጎዱ መሰረተ-ልማቶችን መልሶ መገንባት እና በግጭቱ ምክንያት ፆታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች ድጋፍ ማድረግ ነው ያሉት ሚኒስተሯ፤ ፕሮጀክቱ በተለይ በግጭትና በጦርነት ምክንያት ከፍተኛ ጉዳት በደረሰባቸው በትግራይ፣ አማራ፣ አፋር፣ ኦሮሚያ እና ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች በተመረጡ 40 ወረዳዎች ቅድሚያ ሰጥቶ ተግባራዊ እየተደረገ ያለ ነው ብለዋል፡፡

በዚህ ፕሮጀክት ከግጭቱ ጋር በተያያዘ ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሰጠውን አገልግሎት ማሻሻል እና ማጠናከር፤ ነባር የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎችን ማጠናከር፤ በጤና፣ ስነ-ልቦና፣ፖሊስና የህግ ድጋፍ ማግኘት ላይ ትኩረት ያደረጉ ስልጠናዎችን መስጠት፤ ፆታዊ ጥቃትን መከላከልና ለመከላከል በሚደረገው ጥረት የባህሪ ለውጥ ማምጣት የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን እንዲሁም ለጥቃቱ ተጋላጭ ወገኖች የማገገሚያ ማዕከላትን እና ጊዜያዊ ማረፊያዎችን የመገንባት ስራን እንደሚያካትት ተናግረዋል፡፡

የዩኒሴፍ ተወካይ አቶ ዳውዳ ጉዊንዶ በበኩላቸው፤ ዮኒሴፍ በኢትዮጵያ ግጭት በተከሰተባቸው አካባቢዎች ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶችን በዘላቂነት እንዲያገግሙ ለማድረግ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ እንደሚያደርግ ገልጸው፤ እስካሁን በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ቤኒሻንጉል እና በሌሎችም ክልሎች ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸውን ሴቶች እያገዘ ሲሆን ይህ ስምምነትም ይበልጥ ያጠናቅረዋል ብለዋል፡፡

ፕሮጀክቱ ከግብ እንዲደርስም ዮኒሴፍ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጎን በመሆን የሥርዓተ ፆታ ጥቃት ለመከላከል ኃላፊነታቸውን እንደሚወጡ ገልጸዋል፡፡

በጤና ጉዳዮች ላይ ትኩረቱን በማድረግ ሰብአዊ አገልግሎት ላይ የሚሰራው ጂፔጎ የተሰኘው ዓለም አቀፍ ግብረ ሰናይ ድርጅት የኢትዮጵያ ተወካይ ወይዘሮ ሸዋ ግርማ በበኩላቸው፤ ይህ ስምምነት ፆታዊ ጥቃት የደረሰባቸውን የህብረተሰብ ክፍሎች ተገቢውን መሰረታዊ አገልግሎቶች እንዲያገኙ የማድረግ አላማ ያለው መሆኑን ገልጸው፤ ለሚቀጥሉት ሁለት አመታት ተግባራዊ በመሆን ፆታዊ ጥቃት ለደረሰባቸው ሴቶች እና ህጻናት ተገቢውን የጤና ፣የስነልቦና እና የህግ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ ለማድረግ እንደሚሰራ ገልጸዋል፡፡

# ብቁ ዜጋን ለመቅረጽ የሚያስችል የቀዳማይ ልጅነት ዕድገት መርሐግብር በአዲስ አበባ ተጀመረ

**ሳሙኤል ወንደሰን**



<u>አዲስ አበባ</u>፡- የነገውን ትውልድ ብቁ ዜጋ አድርጎ ለመቅረጽ “የቀዳማይ ልጅነት ዕድገት ፕሮግራም” የተሰኘ ሳምንታዊ የንቅናቄ መርሃ ግብር በአዲስ አበባ ተጀመረ፡፡

የአዲስ አበባ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ንቅናቄውን በትናንትናው እለት ባስጀመሩበት ወቅት እንደተናገሩት፤ በቀዳማይ ልጅነት ዕድገት ፕሮግራም ከዜሮ እስከ ስድስት ዓመት ያሉ ህጻናት የሚካተቱ ሲሆን፤ ፕሮግራሙ የህጻናቱ ጤንነት እንዲጠበቅ፣ ሰብዕና እና ሞራል እንዲገነባ የሚረዳ ነው፡፡ ህጻናት በሁሉም ረገድ የበለጸጉ እንዲሆኑ ያስችላል። ይህም የህጻናት ክብካቤ ማዕከላት የነገውን ትውልድ ብቁ ዜጋ አድርጎ ለመቅረጽ የማይተካ ሚና እንዲጫወቱ የሚያስችል ነው ብለዋል።

የቀዳማይ ልጅነት ዕድገት ፕሮግራም ከድህነት ነፃ የሆነች አገር በመገንባት ረገድ ጉልህ ሚና ይጫወታል ያሉት ከንቲባዋ፤ ይህም ሙሉ በሙሉ በሚተገበርበት ወቅት ህጻናት አሁን ከሚማሩበት የተለመደ የትምህርት አሰጣጥ ሂደት ወጥተው በዓለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መንገድ እንዲማሩ ያስችላል ብለዋል።

የፕሮግራሙ ዋና ዓላማ በሁሉም ረገድ የበቁ ሀገር ተረካቢ ህጻናትን መፍጠር መሆኑን የጠቆሙት ከንቲባ አዳነች፤ በመጪዎቹ ሶስት ዓመታት በቀዳማይ ልጅነት ልማት ፕሮግራም አማካኝነት አዲስ አበባን ለሕጻናት የተመቸች ለማድረግ የተለያዩ የሕግ ማዕቀፎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ፍኖተ ካርታና ዝርዝር ዕቅዶች መዘጋጀታቸውን ገልጸዋል።

በመጪዎቹ ሶስት ዓመታት እስከ 12 ሺህ የሚደርሱ የህጻናት መጫወቻዎች፣ አንድ ሺህ ገደማ የሚሆኑ ልዩ ልዩ የህጻናት እንክብካቤ ማዕከላት በመንግሥት፣ በሕብረተሰቡና በግሉ ዘርፍ ትብብር ማስፋፊያ እንደሚደረግ ተናግረው፤ ፕሮግራሙን ስኬታማ ለማድረግ ቤት ለቤት ለወላጆች ምክርና ድጋፍ የሚሰጡ አምስት ሺህ ሰራተኞች ተቀጥረው እንደሚሰማሩ አስታውቀዋል።

ከነዚህም ውስጥ አንድ ሺህ 400 የሚሆኑት በከተማዋ በሚገኙ ሁሉም የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የሶስት ወራት ስልጠና ወስደው መመረቃቸውን አስታውቀዋል።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ በበኩላቸው፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ያስጀመረው የቀዳማይ ልጅነት ዕድገት ፕሮግራም አስተዳደሩ ለህፃናት ልዩ ትኩረት መስጠቱን ያሳያል። ፕሮግራሙ ውጤታማ እንዲሆን ተመራቂ ባለሙያዎች በሀገር ወዳድነት ስሜት ሊሰሩ ይገባል ብለዋል።

አገርን መውደድ የሚገለፀው ለህፃናት ልዩ ትኩረት በመስጠት ጭምር ነው ያሉት ሚኒስትሯ፤ በሂደቱ የሚያጋጥሙት ችግሮች ለአገር ግንባታ እና ለነገ ትውልድ መሆኑን በመገንዘብ ተነሳሽነትን ማሳደግ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

በተለይ በፕሮግራሙ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች ትኩረት በመሰጠቱ ከተማ አስተዳደሩን አመስግነው፤ ሁሉም ዜጋ ሀገር ወዳድ መሆኑን ለማረጋገጥ የነገ ተስፋ ህፃናት ላይ ሊሰራ ይገባል ብለዋል።

በህፃናት ላይ ኢንቨስት ማድረግ ለሀገር ግንባታ ጉልህ ሚና አለው ያሉት ደግሞ የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰ ናቸው።

እንደ ዶክተር ሊያ ገለፃ፤ ብቁ የአገር ተረካቢ ለማፍራት በህፃናት ላይ ኢንቨስት ማድረግ ያስፈልጋል። የቀዳማይ ልጅነት ዕድገት ፕሮግራምም የዚሁ አካል በመሆኑ ለቀጣይ ትውልድ ግንባታ ጉልህ ሚና አለው። ይህም ተግባራዊ እንዲሆን ከተማ አስተዳደሩ እየሰራ ያለው ሥራ ሊበረታታ ይገባል ብለዋል።

በዚህ ሂደት ጤና ሚኒስቴር በርካታ ስራዎችን እየሰራ ነው ያሉት ዶክተር ሊያ፤ ሚኒስቴሩ ህፃናት በወቅቱ ክትባት እንዲያገኙ እና ልጆች በአካል፣ በስብዕና እና በአዕምሮ ብቁ እንዲሆኑ እየሰራ ነው። ይህም ቀጣይ ትውልድን ለመገንባት የራሱ የሆነ አስተዋጽኦ አለው ብለዋል።

ከንቲባ አዳነች አቤቤ የከተማ አስተዳደሩ በክበበ ፀሃይ ያስገነባውን የህጻናት ክሊኒክ እና በልደታ ክፍለ ከተማ የተገነባውን የህጻናት ማቆያ ማዕከል በትናንትናው ዕለት መርቀው ሥራ አስጀምረዋል፡፡

# የአገራትን ግንኙነት ለማጠናከር በጥበብና ባህል ነክ ጉዳዮች ላይ በጋራ መሥራት ይገባል

**ልጅዓለም ፍቀሬ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- የአገራትን የሁለትዮሽ ግንኙነት ለማጠናከር በጥበብና ባህል ነክ ጉዳዮች ላይ በጋራ መስራት ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳለው በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የውጭ ግንኙነትና ሰላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አባል አምባሳደር ዲና ሙፍቲ ተናገሩ፡፡

የተባበሩት አረብ ኢምሬትስ እና ለማ ጉያ ፋውንዴሽን ጥበብን ማስተዋወቅ እና ጠብቆ ለትውልድ ማስተላለፍ በሚቻልባቸው ጉዳዮች ዙሪያ ሰኔ 13 ቀን 2015 ዓ.ም የጋራ የምክክር መድረክ አካሂደዋል፡፡

አምባሳደር ዲና ሙፍቲ በምክክር መድረኩ ላይ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያና የተባበሩት አረብ ኢምሬትስ በባህልና ጥበብ ነክ ጉዳዮች ላይ በጋራ ለመስራት የምክክር መድረክ ማዘጋጀታቸው የአገራቱ የሁለትዮሽ ግንኙነት ለማጠናከር ጉልህ ሚና አለው፡፡

ባህልንና ጥበብን በአገራቱ መካከል እርስ በርስ ማስተዋወቅና ጠብቆ ለትውልድ ማስተላለፍ በራስ መተማመን ለማዳበርና ፈጠራን ለማበረታታት ያግዛል ያሉት አምባሳደር ዲና፤ በተጨማሪም የዜጎችን የአኗኗር ዘይቤ በእጅጉ እንዲሻሻል ያግዛል ብለዋል፡፡

እንደ አምባሳደር ዲና ገለጻ፤ በባህልና ጥበብ ላይ መስራት የራስን እሴት፣ ወግ፣ ልማድ እንዲሁም የአገርን ተፈጥሮዊና ሰው ሰራሽ ሀብትን ለማስተዋወቅና ሃሳብን ለመግለጽ እድል ይሰጣል፡፡ በተጨማሪም የሰዎችን ችግር የመፍታት አቅምን ያሳድጋል፡፡

አምባሳደር ዲና የኪነ- ጥበብና የባህል ግንኙነት እንዲጎለብት ማድረግ ልማትን ለማፋጠን ትልቅ ድርሻ አለው ብለዋል፡፡



**አምባሳደር ዲና ሙፍቲ**



**አርቲስት ሰላማዊት ለማ**

የኢትዮጵያና የአረቡ ዓለም ግንኙነት በቅርብ የተጀመረ ሳይሆን ነቢዩ መሐመድ ወደ ኢትዮጵያ በመጡ ጊዜ የተጀመረ መሆኑን ያስታወሱት አምባሳደር ዲና፤ ኢትዮጵያ በቀይ ባህር አካባቢ ያለች ሀገር እንደመሆኗ መጠን በኢኮኖሚ ፣በማህበራዊና በግብርናው ዘርፍ ተሳስሮ ለማደግ እንደሚያግዝ ጠቁመዋል፡፡

የለማ ጉያ ፋውንዴሽን መስራችና ፕሬዚዳንት አርቲስት ሰላማዊት ለማ በበኩሏ፤ የመድረኩ ዋና ዓላማ ባህልና ጥበብ ማስተዋወቅና ጠብቆ ለትውልድ ማስተላለፍ ነው ፡፡ መድረኩ የሁለቱን አገራት የህዝብ ለህዝብና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የሚያሳድግ መሆኑን ተናግራለች፡፡

በአገራት የባህል ለውውጥ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት በማጠናከር ለዜጎች የሥራ እድል ለመፍጠር ያስችላል ያለችው ፕሬዚዳንቷ፤ የተባበሩት አረብ ኢምሬትስ በንግድ፣ በኢንቨስትመንት፣ በባህል፣ በትምህርት እንዲሁም በግብርናው ዙሪያ ከኢትዮጵያ ጋር አብረው ስለሚሰሩ በባህልና በጥበቡም ትስስሩ ከተጠናከረ በዘርፉ ውጤታማ መሆን ይቻላል ብላለች፡፡

እንደ አርቲስት ሰላማዊት ገለጻ፤ ለማ ጉያ ፋውንዴሽን በኢትዮጵያ በኩል አገርን ወክሎ እየሰራ ነው፡፡ የዓለም ህዝቦችን በኪነ- ጥበብና በባህል ግንኙነት እንዲተሳሰሩ ማድረግ የፋውንዴሽኑ ራዕይ ነው፡፡

የባህል ልውውጥ ማድረግ የሁለትዮሽ ግንኙነቱን ከማጠናከር ጎን ለጎን ቅርሶች ለመጠበቅና ለትውልድ ለማስተላለፍ ወሳኝ ሚና እንደሚኖረው አርቲስት ሰላማዊት ገልጻለች፡፡

በኢትዮጵያ የተባበሩት አረብ ኤምሬትስ ኤምባሲ የፖለቲካ፣ኢኮኖሚና የሚዲያ ዘርፍ ኃላፊ ሚስተር ታላል አል አዚዚ በበኩላቸው ፤ የተካሄደው መድረክ የባህል ግንኙነት እንዲዳብር ከማድረጉም በላይ በመሪዎችና በሕዝብ መካከል ጠንካራ ወዳጅነት እንዲኖር ያደርጋል ብለዋል፡፡

በኢትዮጵያና በተባበሩት አረብ ኢምሬትስ የቆየ ታሪካዊ ግንኙነት እንዳለ የተናገሩት ኃላፊው፤ በባህልና በኪነ-ጥበብ ዘርፍ በጋራ መስራት ግንኙነቱን ይበልጥ እንዲጠናከር ያደርገዋል ነው ያሉት፡፡

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ ሁለቱ አገራት በጋራ መስራታቸው ግንኙነትን ከማጠናከር ባሻገር ለልምድ ልውውጥ፣ ፈጠራ ለማበረታታት ፣ለሥራ እድል ፈጠራ ፣ ባህልንና ቅርስን ለማስተዋወቅ ዕድል ይፈጥራል፡፡

## ዜና

# "ለዜጎች የሚደረግ እርዳታን የማቆም ውሳኔ ፖለቲካዊ አንድምታ ያለበት ነው"

**- አምባሳደር ጥሩነህ ዜና**
**የቀድሞ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽነር**



**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- ለዜጎች የሚደረግ የሰብዓዊ ድጋፍን የማቆም ውሳኔ ፖለቲካዊ አንድምታ ያለበት ነው ሲሉ የቀድሞ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽነር ገለጹ።

የቀድሞ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽነር አምባሳደር ጥሩነህ ዜና ከሰብዓዊ ድጋፍ ክልከላ ጋር ተያይዞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሰብዓዊ እርዳታ ለተራበና በረሀብ ለተጎዱ ህዝቦች የሚላክ በመሆኑ እርዳታ የማቆም ውሳኔ ፖለቲካዊ አንድምታ ያለበትና ሥርዓትን ያልተከተለ እርምጃ ነው።

እንደ አምባሳደር ጥሩነህ ገለጻ የሚመለከተው አካል በእርዳታ አሰጣጡ ላይ ስህተት ካለ በማረም ፤አጥፊውን በመቅጣት እንዳይደገም አደርጋለሁ በማለት ተገቢውን ምርመራ በማድረግ ላይ ነው። በመሆኑም ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት የሌለውንና ያላጠፋውን ህዝብ መቅጣት ተገቢ አይደለም።

እርምጃው በጦርነት ወቅት የተጎዳና በችግር ላይ የሚገኙትን ዜጎች የሚጎዳ በመሆኑ የዓለም አቀፍ ህግ አይፈቅደውም ያሉት አምባሳደር ጥሩነህ፤ ሰብዓዊ እርዳታ ሰጪዎች ፍላጎታቸውን ለማሳካት የሚያቅማማውን አገርና ህዝብ ለመጉዳት የሚወሰድ እርምጃ ነው ብለዋል።

በዓለም አቀፉ ህግ በአንድ አገር ላይ መሰል ችግሮች በሚያጋጥሙበት ወቅት አጥፊውን መሰረት ያደረገ ውሳኔ መጣል እንዳለበት ተቀምጧል። በዚህም አጥፊውንም ያላጠፋውንም የሚቀጣ ውሳኔ መቀመጥ እንደሌለበት ቀደም ሲል በነበሩ ዓለም አቀፍ ጉባኤት ላይ መግባባት የተደረሰበት መሆኑን አስታውሰዋል።

በጉዳዩ ዙሪያ መንግሥት ተገቢውን ትኩረት በመስጠት በዓለም አቀፍ ፎረሞች ላይ ውሳኔው ትክክል እንዳልሆነ ማስረዳት አለበት። በመሆኑም ዜጎች ምንም አይነት ጥፋት ያላጠፋ መሆኑንና ተገቢ ውሳኔ አለመሆኑን መገለጽ ያለበት ጉዳይ መሆኑን አመላክተዋል።

በሌላ በኩል ውሳኔው መጀመሪያ መደረግ እንደሌለበት ገልጸው ፤ አሁንም ቢሆን በፍጥነት መለወጥ የሚገባው ውሳኔ ነው። የዚህም በተለይም የተባበሩት መንግሥታት የዚህን ጉዳዮች ከዓለም አቀፍ ስምምነቶችና በምዕራባውያን ግፊት ከመርሁ ውጪ እየሄደ መሆኑን ተናግረዋል።

በቅርቡ ሰብዓዊ እርዳታ ላልታለመለት ዓላማ ውሏል በሚል ክስ የዓለም ምግብ ድርጅትና የአሜሪካው ተራድኦ ድርጅት ድጋፋቸውን ማቋረጣቸውን ተከትሎ መንግስት ውሳኔው ፖለቲካዊ ዓላማ ያለውና ፕሮፓጋንዳ ከመሆኑም በላይ ተረጂ ዜጎችን ለጉዳት የሚዳርግ እንደሆነ መግለጹ ይታወሳል።

# የምግብ ሥርዓትና ሥነ-ምግብ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

አሁን ላይ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተቋቋመው የኢትዮጵያ የምግብ ሥርዓትና ስነምግብ የሚኒስትሮች ስቲሪንግ ኮሚቴ በተበታተነ መልኩ ሲከናወኑ የነበሩ ሥራዎችን በተቀናጀ መልኩ ለመሥራትና አገራዊ አቅሞችን አስተባብሮ ለውጥ ለማምጣት ያግዛል ብለዋል፡፡

ኢ.ኤ.አ በ2018 እንደ አገር የመጀመሪያው የሥርዓት ምግብና ሥነምግብ ስትራቴጂ እንዲወጣ መደረጉን ያመለከቱት ሚኒስትሯ፤ ከሥርዓተ ምግብ ጋር በተገናኘ የሚከሰተውን መቀንጨር ለመግታትም በ2016 የሰቆጣ ቃልኪዳን እንዲወጣ ተደርጎ ሥራዎች ሲሠሩ ቆይተዋል ብለዋል፡፡ የሚኒስትሮች ስትሪንግ ኮሚቴ መቋቋም ቀደም ብለው በተለያዩ ተቋማት የተጀመሩ ሥራዎችን በተቀናጀ መልኩ ተቋማዊ አድርጎ ለመተግበር የሚያስችል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የግብርና ሚኒስትሩ ዶክተር ግርማ አመንቴ በበኩላቸው ፤ የምግብ ዋስትና አለመረጋገጥ እንደ አገር አንገታችንን እንድንደፋ የሚያደርገን አሳሳቢ ችግር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ምርት ከማምረት በላይ ነው ያሉት ሚኒስትሩ፤ የተመረተውን ምርት ከብክነት መከላከልና የትኛው ምግብ ምን ይዘት አለው፤ በምን መልኩ እንጠቀመው በሚለው ላይም ግንዛቤ ማስጨበጥ ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ ለምግብ ሥርዓትና ሥነምግብ ችግሮችን ዘለቄታዊ መፍትሔ ለመስጠት በትኩረት መሥራት እንደሚገባ ገልጸው፤ በቀጣይነት በመንግሥትም ሆነ በልማት አጋሮች የሚሠሩ የልማት ሥራዎች ከዚህ ፍኖተ ካርታ ጋር የሚናበቡ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል፤ የዚህ ኮሚቴ መቋቋም የተቋም አጥር ሳይገድበን ያሉ አቅሞችንና ፀጋዎችን አስተባብሮ ለመጠቀም ያስችላል ብለዋል፡፡

የስትሪንግ ኮሚቴው የኢትዮጵያን የምግብ ሥርዓት ሂደት፣ የምግብና የተመጣጠነ ምግብ ስትራቴጂ እና የሰቆጣ ቃልኪዳንን ለማስተባበርና ለመምራት፣ ፖሊሲዎችንና የሕግ ማዕቀፎችን ለመምራት የተቋቋመ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን፤ የክልል መንግሥታትን የመደገፍ፣ አተገባበሩን የመከታተልና የመገምገም ተግባራትን ያከናውናል።

በተጨማሪም ፈንድ በማፈላለግና ለሥራው በጀት እንዲመደብ በመከታተል የኢትዮጵያ የምግብ ሥርዓትና ሥነምግብ ሥራ በአገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ ለውጤት እንዲበቃ ይሠራል።

የኢትዮጵያ የምግብ ሥርዓት እና ሥነምግብ የሚኒስትሮች ስቲሪንግ ኮሚቴ 15 ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶችን ያካተተ ሲሆን በግብርናና ጤና ሚኒስትሮች ይመራል ተብሏል።

የኢትዮጵያ የምግብ ሥርዓት እና ሥነምግብ ትራንስፎርሜሽን አጀንዳ ቀረጻ ሂደት ላይ ከ120 በላይ ባለሙያዎችና ከ40 የተለያዩ ተቋማት ፣ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የምርምር ተቋማት እና የተባበሩት መንግሥታት የተለያዩ ኤጀንሲዎች መሳተፋቸው የተገለጸ ሲሆን፤ ምርትና ምርታማነትን መጨመር፣ የገጠር ኑሮን ማሻሻል፣ የምግብ ዋጋ ንረትን ማረጋጋት እና ጤናማ ምግቦችን አመጋገብ ማሻሻል እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠበቅን ዓላማ ያደረገ መሆኑ ተመላክቷል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## በሐሰት ክስ የኢትዮጵያን ሥም ማጠልሸት አይቻልም!

እንደ አገር በምግብ እህል ራሳችንን ለመቻል የጀመርናቸው ጥረቶች በብዙ ልፋትና ርብርብ ፍሬ ማፍራት በጀመሩበት፤ ዓለም አቀፍ እውቅና አግኝተው የመገናኛ ብዙኃን አጀንዳ እየሆኑ በመጡበት ማግስት አገርና መንግሥትን ከሁሉም በላይ በዘርፉ እየተመዘገቡ ያሉ ስኬቶችን የማጠልሸት ትርክቶች መሰማት ከጀመሩ ውለው አድረዋል።

በቅርቡ የርዳታ ስንዴ ተሰረቀ በሚል የተጀመረው ይህ በመረጃና በበቂ ማጣራት ላይ ያልተመሰረተው ትርክት፤ በአንዳንድ መገናኛ ብዙኃን ያልተገባ አቅም ገንብቶ፤ በችግር ውስጥ ያሉ ድጋፍ ፈላጊዎች የሚያስፈልጋቸውን ርዳታ በወቅቱ እንዳያገኙ ትልቅ ፈተና ሆኗል።

የትኛውም ማኅበረሰብ የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሠራሽ ችግሮች በሚያጋጥሙበት ወቅት ፤ ለዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ የርዳታ ጥሪ የማቅረብና የመረዳት መብት አለው። ይህ መብቱ በዓለም አቀፍም ሆነ በሞራል ሕግ የተደገፈ ነው። ዋና ዓላማውም በችግር ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን ሕይወት ከጥፋት መታደግና ነገዎቻቸው እንዳይጨልሙ ማድረግ ነው።

እንዲህ ዓይነት ክስተቶች በየትኛውም የዓለም ክፍል በተለያዩ መንገዶች ሊከሰቱ ይችላሉ፤ ችግሩን ተቋቁሞ የመሻገሩ እውነታ እንደየአገሩ የኢኮኖሚ አቅምና የአደጋ ዝግጁነት የሚሰላ ቢሆንም፤ የሌሎችን ድጋፍ የመሻቱ እና በአደባባይ ከፍ ባለ ድምጽ የማሰማቱ ሁኔታ ግን የተለመደና ወደፊትም ሊቀጥል የሚችል ነው። በዚህ ሂደትም ብዙ ያደጉም ሆኑ ድሀ የሚባሉ አገራት አልፈውበታል።

ችግሮቹ የሚፈጥሩት ተመጽዋችነት በራሱ ብሔራዊ የልብ ስብራት የሚፈጥር ቢሆንም፤ የርዳታ ጥሪዎች በአደጋ ውስጥ የሚገኙ ሰዎችን ሕይወት ከማትረፍ አንጻር፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚደረጉ ናቸው። ይህንን አለማድረግ በራሱ እንደ አንድ ትልቅ ወንጀል የሚወሰድ፤ በዓለም አቀፍ ሕግም የሚያስጠይቅ ጭምር ነው።

የኢትዮጵያ መንግሥትም ባለፉት አምስት ዓመታት በአገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች ከተፈጠሩ የሰላም እጦቶች፤ ከኮቪድ፤ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ከተካሄደው ጦርነት እና ከተለያዩ የተፈጥሮ አደጋዎች ጋር በተያያዘ ሰፊ ቁጥር ያላቸው ዜጎች በችግር ውስጥ እንደሚገኙ ለዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ በማሳወቅ የርዳታ አቅርቦቶች ለተረጂዎች ያለ ብዙ ውጣ ውረድ የሚቀርቡበትን የተመቻቸ ሁኔታ ፈጥሯል።

በዚህም ዓለም አቀፉን የምግብ ድርጅት / ወርልድ ፉድ ፕሮግራም / እና የአሜሪካ ተራድኦ ድርጅት ን /ዩ ኤስ ኤይድ/ን ጨምሮ የተለያዩ የርዳታ ተቋማት ወደ አገር ውስጥ በመግባት ከሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት ጋር በመተባበር በራሳቸው ተቋማዊ መዋቅር የርዳታ አቅርቦቶችን ለተረጂዎች ሲያደርሱ ቆይተዋል። በዚህም የብዙ ዜጎችን ሕይወት መታደግ ተችሏል።

አገሪቱ ከነበረችበት ተጨባጭ ሁኔታም አንጻር መንግሥት ባልተቆጣጠራቸው አካባቢዎች፤ በርዳታ እህል አቅርቦትና አጠቃቀም ዙሪያም ብዙ ጥያቄ የሚያስነሱ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ በችግሮቹም ዙሪያም በወቅቱ ሰሚ ያጡ ከፍ ብለው ሲደመጡ የነበሩ ድምጾች ነበሩ። የሚመለከታቸው አካላትም ለድምጾቹ ተገቢውን ምላሽ መስጠት አቅቷቸው ዝምታን መምረጣቸው ይታወሳል።

ይህ እውነት የአደባባይ ምስጢር በሆነበት፤ ከዝምታው በስተጀርባ የተፈጠሩ ጫናዎች አገርና ሕዝብን ብዙ ዋጋ ባስከፈሉበት ማግስት፤ መንግሥት በብዙ ተግዳሮቶች ውስጥ ሆኖ በስንዴ ምርት ዙሪያ የዓለም አቀፉን ኅብረተሰብ ትኩረት የሳበ የስኬት ታሪክ ትርክት ውስጥ ሲገባ የተፈጠረው «የስንዴ ተሰረቀ ጩኸት» አንደምታው ለተረጂዎች ከመቆርቆር የመነጨ ስለመሆኑ አጠያያቂ ነው።

በአንድ በኩል 70 ከመቶ የሚሆነው የእርዳታ አቅርቦት በርዳታ ተቋማቱ ተቋማዊ መዋቅር ለተረጂዎች በሚከፋፈልበት፤ ከዚያም በላይ ተሰረቀ በሚባለው የርዳታ አቅርቦት ዙሪያ የሚመለከታቸው አካላት በጋራ የማጣራት ሥራዎችን ባልሠሩበትና በውጤቱ መስማማትም ሆነ አለመስማማታቸው ባልታወቀበት ሁኔታ «የተሰረቀን ድምጽ» ከፍ አድርጎ ማሰማት ተገቢም፤ ተቀባይነት ያለውም አይሆንም፡፡

በተለይም ዓለም አቀፉ የምግብ ድርጅት በተጨባጭ ማስረጃ ያልተደገፈ ሪፖርትን መሠረት በማድረግ ለተረጂዎች ይደርስ የነበረውን የርዳታ አቅርቦት ማቋረጡ ካለበት ዓለምአቀፋዊ ኃላፊነት አንጻር ከፍያለ የሕግና የሞራል ተጠያቂነት የሚያስከትል ነው። በተረጂዎችም ሕይወት ላይ የመፍረድ ያህል ነው።

ሌሎች የተራድኦ ድርጅቶችም ቢሆኑ ቀደም ባሉት ጊዜያት ካለርዳታ አቅርቦትና አጠቃቀም ጋር በተያያዘ ሰፊ ጥያቄዎች ሲነሱ ለጥያቄዎቹ ምላሽ ለመስጠት ፍቃደኛ ሳይሆኑ ቀርቶ፤ አሁን ላይ በተገቢው መንገድ የማጣራት ሂደትን ያላለፈ ሪፖርት በማውጣት አገርና መንግሥትን ባልተገባ መልኩ በመወንጀል ላይ መጠመዳቸው፣ ከተቋቋሙበት ዓላማ አንጻር ተጠያቂነትን የሚያስከትል ያልተገባ ተግባር ነው።

በተለይም እንደ አገር በምግብ እህል ራሳችንን ለመቻል እያደረግናቸው ያሉ ጥረቶች በብዙ መንገድ ተስፋ ሰጪ በሆኑበት፤ ከሁሉም በላይ የበጋ ስንዴ ልማት በብዙ ስኬት የዓለም አቀፉን ኅብረተሰብ ትኩረት እየሳበ ባለበት በዚህ ወቅት ኢትዮጵያን «በርዳታ ስንዴ ስርቆት» ለመወንጀል የሚደረገው እንቅስቃሴ፤ ስኬትን ለማጠልሸት የሚደረግ ሙከራ ቢሆንም መሠረቱ ሐሰት ነውና የሚሳካ አይሆንም!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ‹‹እርቅ እንባ ያደርቅ››

ሜላት ኢያሱ

አገሬው ዘመናትን በተሻገረው አብሮነቱ የሚያጋጥሙትን ማኅበራዊ ችግሮች ሁሉ እየፈታ አገሩን ያጸናበት የራሱ ባህላዊና ሃይማኖታዊ እሴቶች አሉት:: ተረቶቹ፣ ምሳሌዊ ንግግሮቹ ወጎቹ ... ወዘተ በዘፈቀደ የሚነገሩ ሳይሆኑ አኗኗሩን እና እሱነቱን በሚገባ የሚገልጹ፤ ማኅበራዊ አወቃቀሩ፣ ስሪቱ ወይም አኗኗሩ ምን መልክ መያዝ እንዳለበት ቅርጽ የሚያስያዙ ናቸው::

ምሳሌዊ ንግግሮቻችን እኛን ይመስላሉ፤ እኛም እነርሱን እንመስላለን:: ከችግሮቻችን የምንወጣባቸውን ቀና መገንገዶች ያመላክቱናል፤ በፍቅር፣ በሰላም እንድንተሳሰር ብርቱ ምክር ይለግሱናል፤ ከላይ ርዕስ አድርገን የተጠቀምነው « እርቅ እንባ ያድርቅ» የሚለው የአበው ብሂል በተለያዩ ጉዳዮች በተለይም በነፍስ መጠፋፋት ምክንያት ዓይንህ ለአፈር የተባባሉና ለበቀል የሚፈላለጉ ሰዎች ቂማቸውን እርግፍ አድርገው ትተው እርቅ እንዲያወርዱ የሚያደርግ፤ ይቅር ባይነትን የሚያስተምር፤ የልብ ስብራትን የሚጠግን ነው::

አባባሉ ተራ ንግግር ሊመስለን ይችላል፤ ነገር ግን የግሪክ ፈላስፎች ከሚናገሯቸው አባባሎች ያልተናነሰ በብዙ መልኩ ሊተነተን እና ሊመነዘር ወደሚችል እውነታ የሚወድስ ምጡቅ አስተሳሰብ ነው:: ይቺ አንድ ዘለላ የቃላት ስብስብ ወይም ሐረግ የተሸከመችው መልዕክት ለብዙዎች መድህን የመሆኗ ነገር አያጠራጥርም:: በየአካባቢው በበዳይና በተበዳይ መካከል ያለውን የጥላቻ ግንብ እየደረመሰች በሕዝቦች መካከል ሰላማዊ መስተጋብር እንዲፈጠር የማድረግ ሚናዋ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም::

እነዚህ ምሳሌያዊ አነጋገሮቻችን ማኅበራዊ ቅርጻችንን በተለያየ መንገድ መልክ አስይዘውታል:: ለምሳሌ ‹‹ወፍ እንደአገሯ ትጮሃለች፤ የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ›› የሚሉትን ብንመከት ለአካባቢያዊ ችግራችን እራሳችን አካባቢዊ መፍትሔ መስጠት እንዳለብን የሚያስገነዝቡና የሚመክሩ ናቸው::

ሩቅ ከመመልከት ይልቅ አጠገባችን ያሉትን በርካታ አማራጮች እየተጠቀምን የእርስ በእርስ ግንኙነታችንን እንድናጠናከር፤ እንደጎረቤቶቻችን ሳይሆን እንደቤታችን ወግና ባሕል እንድንኖር የሚረዱን ናቸው:: የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ለማሳያነት ተጠቀምሁ እንጂ በሁሉም ቋንቋዎቻችን ተመሳሳይ ይዘት ያላቸው አባባሎች አሉ::

ምሳሌያዊ ንግግሮቻችን እሴቶቻችንም ናቸው፤ እሴቶቻችን ደግሞ ኢትዮጵያዊነታችንን ቁልጭ አድርገው የሚያሳዩ መገለጫዎቻችን ናቸው፤ ሠርተውናል:: ፍቅርን፣ ሰላምን፣ እርቅን፣ መተዛዘንን፣ መደጋገፍን፣ መተማመንን፣ አንድነትን ወዘተ እየሰበኩ ማኅበራዊ ግንኙነታችን በጠንካራ መሠረት ላይ እንዲቆም አስተዋጽኦ አበርክተውልናል:: ሃይማኖታዊ እሴቶቻችንም ቢሆኑ እንዲሁ የህሊናችንን ጉድፍ አጽድተው ግላዊ ባህሪያችንም ሆነ ማኅበራዊ ቅርርባችን የተቃና እንዲሆን አስችለውናል::

እኛ ኢትዮጵያውያን ከጎረቤቶቻችንም ሆነ ከተቀረው ዓለም የምንለየው ለሃይማኖታዊና ባህላዊ እሴቶቻችን ዋጋ የምንሰጥ ሕዝቦች በመሆናችን ነው:: ያ ባይሆን ኖሮ ከባዕድ አገር እየተነሳ ሱማሌን፣ የመንን፣ ሱዳንን ፣ ሶሪያን ለእርስ በእርስ ግጭት የዳረጋቸውና ምስቅልቅላቸውን ያወጣቸው አውሎ ነፋስ እኛንም ባፈራረሰን ነበር::

ከዓመታት በፊት በሰሜኑ የአገራችን ክፍል የተፈጠረውን ጦርነት መነሻ አድርገው የተዛቡ መረጃዎችን በማስተላለፍ እና የአንድ ወገን ተቆርቋሪ መስለው በመቅረብ አብሮነታችንን ለማፈራረስና ሰላማችንን ለማደፍረስ ምን ያህል እንደደከሙ የታዘብነው ሐቅ ነው::

ዛሬ ኢትዮጵያ ከነበረችበት ቀውስ ወጥታ ወደ ቀደመው ሰላሟ ለመመለስ አበረታች እንቅስቃሴ እያደረገች ትገኛለች:: ‹‹ወፍ እንደአገሯ.... እንጂ›› እንደ ሂውማን ራይት ዋች ስለማትጮህ የጀመርነውን የሰላም ንግግር እንደአገራችን የሽምግልና ባህል እያስኬድን ለችግራችን መፍትሔ እናስቀምጣለን እንጂ ባዕዳን በሚቀዱልን ቦይ አንፈስም፤ ሰላማችንም ወደ ኋላ አይመለስም::

እርግጥነው ጦርነት በተካሄደባቸው አካባቢዎች የሚኖሩና በዚህም በዚያም ወገን ያሉ በርካታ ንጹኃን ዜጎቻችን ጉዳት ደርሶባቸዋል:: በትግራይ፣ በአፋር በአማራ ክልል ዜጎች በግፍ ተገድለዋል፣ ንብረታቸው ወድሟል፣ ተፈናቅለዋል:: ለጠፋው ጥፋት አንዱ አንዱን ይወቅሳል፣ አንዱ ሌላውን ይከሳል:: ግን በሁሉም ወገን ቆሞ ያጠፋውም ሆነ የጠፋው የእኛው ናቸው::

**አሁን የጦርነት ምዕራፍ ተዘግቶ የሰላም አማራጭ እየታየ ያለበት ወቅት በመሆኑ ገርበብ ብሎ የተከፈተው በር በደንብ ተከፍቶ በሁለቱም ክልሎች የሰላም አየር እንዲናኝ ተመክሯል**

‹የገደለው ባልሽ የሞተው ወንድምሽ ኀዘንሽ ቅጥ አጣ ከቤትሽ አልወጣ›› እንደተባለው ዓይነት ነው:: የቤታችንን ችግር መፍታት ያለብን እኛው ቤተኞቹ እንጂ እንደሂውማን ራይት ዎች ዓይነቶቹ የሩቅ ተመልካቾች አይደሉም:: ‹‹ማን ይናገር የነበረ፤ ማን ያርዳ የቀበረ›› እንዲሉ በቅርብ ስላሉ ቤተሰቦቻችን ጉዳት ለእኛ ለባለጉዳዮቹ ሂውማን ራይት ዎች ሊነግረን ባልተገባ ነበር::

የት ምን ተከሰተ? ምን ያህል ሰው ሞተ? ምን ያህል ንብረት ወደመ? የሚለውን ዛሬም ከእኛው ከኢትዮጵያውያንና ከአካባቢው ነዋሪዎች በላይ የዓይን እማኝ ሆኖ ሊናገር የሚችል የለም:: የሁሉም ዜጎቻችን ጉዳት ጉዳታችን ነው:: የሂውማን ራይት ዎች ወደ አንድ ወገን ያዘነበለ ሪፖርት እና ‹‹አዛኝ ቅቤ አንጓችነት›› የጀመርነውን ሰላማዊ ንግግር ለማደናቀፍ የታሰበ ሴራ እንጂ ከእኛ በላይ ለእኛ በማሰብ አይደለም::

አሁን ኢትዮጵያውያን በደልን ከመቁጠር ወጥተን እንደወግ ባሕላቸው ይቅር እየተባባልን ያለንበት ሰዓት ነው:: በቅርቡ በትግራይ ክልል ጊዜዊ አስተዳደር ፕሬዚዳንት በአቶ ጌታቸው ረዳ የሚመራ ልዑክ ወደ አመራ ክልል በመሄድ የተጀመረውን የሰላም ንግግር ማስቀጠል በሚቻልባቸው ጉዳዮች ላይ ከአማራ ክልል ፕሬዚዳንት ዶክተር ይልቃል ከፋለ እና ከኅብረተሰቡ ተወካዮች ጋር መምከሩ የሚታወስ ነው::

በውይይቱም ዋጋ የማይጠይቅ ሰላማዊ ንግግር እያለ በተፈጠረው ጦርነት ብዙዎች ዋጋ መክፈላቸው የሚያስቆጭ እንደሆነ ተነስቷል:: በፖለቲካ አመራሮች በኩል ያሉ ልዩነቶች ከሕዝቡ በታች እንደሆኑም ተጠቅሷል:: አሁን የጦርነት ምዕራፍ ተዘግቶ የሰላም አማራጭ እየታየ ያለበት ወቅት በመሆኑ ገርበብ ብሎ የተከፈተው በር በደንብ ተከፍቶ በሁለቱም ክልሎች የሰላም አየር እንዲናኝ ተመክሯል::

ከሰላም ውጪ ሌላ አማራጭ ባለመኖሩ ልዩነቶችን በሰላማዊ ንግግርና በሕግ አግባብ መፍታት አማራጭ የሌለው ጉዳይ እንደሆነ፤ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱ ወደነበረበት እንዲመለስ፤ የትራንስፖርት እንቅስቃሴውና የንግድ ትስስሩ እንዲጀመር፤ በፖለቲካ አመራሩ የተጀመረውን የሰላም ግንኙነት የሃይማኖት አባቶች፣ የአገር ሽማግሌዎች በተለይም በሁለቱ ክልሎች አዋሳኝ ያሉ ሕዝቦች አጠናክረው ሊቀጥሉት እንደሚገባ ተመክሯል::

እንግዲህ ችግሮችን እንዲህ ቁጭ ብሎ መነጋገር፣ እርቅማውረድና ሰላም መፍጠር ነባር እሴታችን ነው:: አባቶቻችን በዚህ መልክ ሠርተው ያስረከቡንን አገር እኛም የእነርሱን አደራ ተቀብለን ለልጆቻችን ማስተላለፍ ይገባናል:: እንነጋገር! እንተራረም! እንታረቅ!

# ነፃ ሃሳብ



ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፣ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፣ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፣ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፣ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፣ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

**በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

# « ፍቅር እስከ መቃብር» እና ሰውመሆን ምንና ምን ናቸው ?

**(የመጨረሻ ክፍል)**

በይደር ወዳቆየሁት የ«ፍቅር እስከ መቃብር» እና የዳይሬክተርና የፕሮዲውሰር የሰውመሆን ጉዳይ ከመመለሴ በፊት «ፍቅር እስከ መቃብር» የተዋጣለት ፊልም እንዲሆን ካለኝ ብርቱ መሻትና ምኞት የተነሳ ከረጅም ልቦለድነት ወደ ፊልም ተቀይረው ከሰመረላቸው ዘመንና ትውልድ ተሻጋሪ ሥራዎች እነ :- “The Lord of the Rings” by J.R.R. Tolkien ፣ “Harry Potter” series by J.K. Rowling ፣ “The Hunger Games” series by Suzanne Collins ፣ “The Da Vinci Code” by Dan Brown ፣ እና “Gone with the Wind” by Margaret Mitchell ማስታወስ እፈልጋለሁ። እነ ሰውመሆን እነዚህ ሥራዎች እንዴት የተዋጣለት ፊልም ሊሆኑ እንደቻሉ ቢመረምሩ ብዙ ያተርፋሉ ብዬ አምናለሁ። ለመንደርደሪያ ያህል ይሄን ካልሁ ወደ ዳይሬክተርና ፕሮዲውሰር ሰውመሆን ልመለስ:-

ሰውመሆን ለቀረጻ እንዲያመች አድርጎ የጻፈውን የመጀመሪያ ፊልሙን በወቅቱ ስም ላላቸው ተዋንያን እንዲተውኑለት ሲሰጣቸው በድፍረት ነበር። ጽሑፉን ያነበቡት ግሩም ኤርሚያስ፣ ዕንቁሥላሴ አገኘሁ እና ይገረም ደጀኔን የመሳሰሉ ዕውቅ ተዋንያን በሀሳቡ ተስማምተው በፊልሙ ተሳተፉ። ተዋንያኑ «ሀሳቡን ወደውት፣ አምነውኝ ነው የሠሩት» ይላል ሰውመሆን። ሰማንያ ሺህ ብር ገደማ ከወጣበት ከዚህ ፊልም ግማሹ የተከፈለው ለዋናው ተዋናይ ግሩም ሲሆን ቀሪውን ሌሎቹ ተዋናዮች መከፋፈላቸውን ያስታውሳል። ፊልሙ አብዛኛው ቀረጻው በአንድ ቤት ውስጥ በመከናወኑም ብዙ ወጪ አላስወጣውም። «862» በሚል ርዕስ ለእይታ የበቃው የሰውመሆን ሥራ ሊያሳካ የሚያስበውን ግብም መትቶበታል።

«ምን እላለሁ መሰለህ? የመጀመሪያ ሥራህ ሁልጊዜ ወይ አነጋጋሪ መሆን አለበት ወይም ደግሞ ትልቅ መሆን አለበት ብዬ አምናለሁ። ፊልሙ በወጣ ጊዜ ሁለት ዓይነት ተመልካች ነበረው። አንዳንዶቹ ‘ይህን ፊልም ከምናይ ፒዛ ብንበላ ይሻላል’ ብለው ይወጣሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ‘እንዴት ዓይነት የተለየ ፊልም ነው’ ብለው ወጡ። በዚህ ግርግር ውስጥ ይህ የሞከርኩት ነገር ዋጋ አግኝቶ፣ ሰዎችም እውቅና ሰጡት። የፎቶግራፍ እውቀቴም እየቀጠለ ሄዶ በደንብ ወደ ሲኒማው ገባሁ» ይላል በመጀመሪያ ፊልሙ ስላገኘው ምላሽ ሲያስረዳ።

በራሱ ፊልም እጁን ያፍታታው ሰውመሆን በመቀጠል በቶም የፊልም ትምህርት ቤት ባለቤት በተሠራው «ፔንዱለም» በተሰኘ ፊልም በሲኒማቶግራፈርነት ተሳተፈ። አዳዲስ እና ያልተለመዱ ነገሮች ሁሌም መሞከር የሚወደው ሰውመሆን በዚህም ፊልም ከዚያ ቀደም በሌሎች ፊልም ሠሪዎች ያልተደፈረ ነገር አድርጓል። እስከዚያን ጊዜ በነበረው አሠራር ፊልም የሚቀረጸው በቪዲዮ ካሜራ አሊያም ለሲኒማ ተብሎ በተሠራ መቅረጫ ነበር። የዘመኑ ቴክኖሎጂ በእጅ የሚንጠለጠሉትን የፎቶ ካሜራዎች ቪዲዮም እንዲቀርጹ አድርጎ አሻሻላቸው። እንዲህ ዓይነት ካሜራዎች ወደአገራችን ቢዘልቁም ደፍሮ ለፊልም የሚጠቀምባቸው አልነበረም። ተስፋዬ ወንድማገኝ በዚያን ወቅት የነበራቸውን ሙከራ ያስረዳል።

«ፔንዱለም የመጀመሪያው የ7D የፊልም ሥራ ነው። 7D የሚባል ካሜራ ከመምጣቱ በፊት በኒከን D90 በሚባል ካሜራ እኔ እና ሰውመሆን/ሶሚክ/ ከተማ እየዞርን እንቀርጻለን። ‘እንደዓይን የሚያይ ነገር በደንብ እንዴት መሥራት እንችላለን? ሌንስ የመጠቀም አቅማችንን እንዴት ነው [የምናዳብረው]’ እያልን በዚያ D90 ትንንሽ ነገሮች እንቀርጽ ነበር። ከዚያ 7D የሚባል ካሜራ ሲመጣ ለመጀመሪያ ጊዜ እኛ ነን ያመጣነው። ሶሚክ ነው ለመጀመሪያ ጊዜ ‘ፔንዱለም’ ላይ የቀረጻበት። እና ከብዙ ትግል በኋላ ነው ያመኑን። በትክክል በፎቶ ካሜራ እንደሚቀረጽ ማለት ነው» ይላል ተስፋዬ።

ሰውመሆን በፊልም ሥራ ውስጥ መስመር ያስያዘኝ የሚለውን «የፀሐይ መውጫ ልጆች» ፊልምን ከመስራቱ በፊት ሲኒማቶግራፈርነቱን አጠናክሮ ቀጥሎበት ነበር። «ኦፕሬሽን አክሱም» የተሰኘ የትግርኛ ፊልም፣ ሄርሞን ሃይላይ ያዘጋጀችውን «ባላገሩ» እና እስካሁን ለዕይታ ያልበቃ በሀሮማያ ዩኒቨርሲቲ የተቀረጸ «ለአንድ ዲግሪ 360 ዲግሪ»ን በተከታታይ ቀረጸ። በመሃል «ይሉኝታ» በተሰኘው የሚካኤል ሚሊዮን ፊልም ላይ በረዳት አዘጋጅነት ተሳትፏል። የዛሬ ስድስት ዓመት ገደማ ቀረጻው በተከናወነው «የፀሐይ መውጫ ልጆች በዝግጅት (ዳይሬክቲንግ)፣ በፊልም ጽሑፍ እና የፊልም ቀረጻ ድርሻዎችን ጠቅሏል። ፊልሙን ፕሮዲዩስ ካደረጉ አምስት ሰዎችም አንዱ ነው።

በቢኒያም ወርቁ የተጻፈው ይህ ፊልም ሰውመሆን እጅ ሲገባ በ28 ገጽ ነበር። ይህን አስፋፍቶ፣ ለፊልም በሚሆን መልኩ አደራጅቶ በ70 ገጽ ለመጻፍ አንድ ዓመት ተኩል እንደወሰደበት ይናገራል። በፊልሙ ላይ ዋና ተዋናይ የነበረው ግሩም ኤርሚያስም አግዞታል። ሰውመሆን «በደንብ ተፈትኜበታለሁ» ስለሚለው «የፀሐይ መውጫ ልጆች» ማብራሪያ አለው።

«ይሄ የመንገድ ጉዞ ፊልም ነው። ሁለት ሰዎች ላይ ብቻ ያተኮረ ስለነበር ጥንቃቄ ይፈልግ ነበር። ‘የፀሐይ መውጫ ልጆች’ የቀረጻ ሂደቱ ከባድ ነበር። ምን መሰለህ? ‘የፀሐይ መውጫ ልጆች’ የወጣበት ገንዘብ እና የፈጀው ጉልበት የሚነጻጸር አይደለም። በገንዘብ ብቻ ለ‘ፀሐይ መውጫ ልጆች’ የወጣው 150 ሺህ ብር ነው። ከዚያ ግን ግሩም ኤርሚያስ፣ ብርቱካን በፍቃዱ፣ ሰለሞን ቦጋለ አልተከፈላቸውም። ማንም ባለሙያ ገንዘብ አልተከፈለውም። እብደት ነበር። ዝም ብለን ወጥተን ነበር ያበድነው።

መንገድ ላይ በጣም ብዙ አስቂኝ፣ ብዙ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ገጥመውናል። አፋር በረሃ ውስጥ ቀርጸናል። አፋር በረሃ ውስጥ ስንቀርፅ አይሱዙ መኪና ነበር ተከራይተን የሄድነው። አይሱዙ ላይ ‘ግሪን ስክሪን’ እያነጠፍን ነበር የምናድረው። ‘እባብ፣ ጊንጥ አለ’ እየተባልን እንደዚህ ነበር የሰራነው ፊልሙን። በጣም ፈታኝ ነበር። ግን ደግሞ ለሁላችንም ትልቅ መሠረት፣ ትልቅ ትምህርት ጥሎ ያለፈ ሲኒማ ነው” ይላል።

ሰውመሆን በዚህ ፊልም የጀመራቸውን አዳዲስ ነገሮችን የመሞከር ሂደት «ዓለሜ» በተባለው ቀጣይ ፊልሙ ላይም አሳይቷል። ስለ ሰውመሆን ሞካሪነት ዳይሬክተሩ ዳዊትም መስካሪ ነው።«ሲኒማቶግራፊ ላይ ስንመጣ ብዙ ጊዜ በአቀራረጽ፣ በተለይ ደግሞ በሙብራት እና ብርሃን አጠቃቀም የራሱን ዘይቤ የፈጠረ ሲኒማቶግራፈር ነው ማለት እንችላለን። በዳይሬክተርነት እንደእኔ ሰውመሆን እየተጓዘ ያለ ዳይሬክተር ነው ብዬ ነው የማስበው።

ብዙ ነገሮችን እየሞከረ፣ እርሱ የሚወደውን እና የሚያምንበትን ዓይነት ነገር ላይ ለመድረስ እየሞከረ ያለ ዳይሬክተር ነው። «የፀሐይ መውጫ ልጆች»ን ምሳሌ ብናደርግ፣ ሌሎቹንም ፊልሞቹንም ብናያቸው ተመሳሳይ ሙከራዎች ውስጥ ያልሆኑ በጣም ብዙ ዓይነት ሙከራዎች እና ሙከራ ብቻ ሳይሆን የሲኒማ ስኬቶችን ጭምር የሚያገኝ ዳይሬክተር ነው።

«የፀሐይ መውጫ ልጆች» ፣ «ዓለሜ»ን ካየኸው ሌሎችም ፊልሞቹን የሚወጡትን፣ የወጡትን ፊልሞችም ካየኻቸው አንደኛ ታሪኩ የሚፈልገውን ነገር በመገንዘብ አዲስ ነገርን ለመፍጠር ይሞክራል። ሁለተኛ ደግሞ ከታሪኩም ውጪ እርሱ እንደፊልም ሰሪ የራሱን ቀለም እና አሻራ ያሳርፋል። ምናልባት እርሱ ቀለምእና ዐሻራ ለማሳረፍ የሚያደርገው ሙከራ ላይሆን ይችላል ግን የሚያደርገው ጥረት ዐሻራውን እንዲያሳርፍ ያደርገዋል ብዬ አስባለሁ።

«ዓለሜ»ን ከወሰድነው በጣም ቀዝቀዝ ባለ ፍጥነት፣ በጣም ጥልቅ የሆነ ታሪክን ለመንገር የሚሞከርበት ፊልም ነው።«የፀሐይ መውጫ ልጆች»ን ደግሞ ካየኸው ፈጠን ባለ ፍጥነት፣ በጣም የሚያስገርም፣ በስሜት ልብ የሚያንጠለጥል አድርጎ ለመንገር የሚሞከርበት ነው። ለሁለቱም እንደ ሲኒማቶግራፈርም፣ እንደዳይሬክተርም ሁለቱም ላይ የሞከራቸውን እና ያደረጋቸውን ነገሮች ስታይ የተለያዩ ግን ለየፊልሞቹ በጣም ተገቢ የሆኑ ነገሮችን የሞከረው» ይላል ዳዊት ስለ ሰውመሆን ሙከራዎች እና ጠንካራ ጎኖች ሲተነትን።

«ዓለሜ» ሰውመሆን በአገር አቀፍ የፊልም ውድድሮች ሽልማቶችን የሰበሰበበት ነው። እርሱም ራሱ «የእኔ ምርጥ ፊልም» ነው ይላል። «ደግሜ እሠራው ይሆን ብዬ ሁሉ የምጠራጠረው ነው» ሲልም ለፊልሙ ያለውን መውደድ በፈገግታ ታጅቦ ያስረዳል።«ከሰኒማቶግራፊ አልፌ ማዘጋጀት አካባቢ ስመጣ ከፍተኛ የሆነ መነሳሳት እፈልጋለሁ። ወደዚያ ታሪክ የሚወስደኝ።«ዓለሜ» መጀመሪያ ተጽፎ ሲመጣ ኮሜዲ የሚመስል ዘውግ ነበረው። ፕሮዲዩሰሯ ዳግማዊት ክፍሌ ትባላለች። ይዛልኝ ስትመጣ መጀመሪያ የእኔ ጥያቄ እንደፈለግሁት እንድጽፈው ትፈቅጅልኛለሽ ወይ? የሚል ነበር ከፈቀድሽልኝ ልሥራው አልኳት።

እንደፈልግኹት እንዳደርገው ፈቀደችልኝ። ሰለሞን ቦጋለ ነበር በጊዜው።«ዓለሜ» ላይ ምንድን ነው ያደረግሁት ? «ዓለሜ» እንደሀሳብ ትንሳኤ ላይ ነው የተሠራው። እውነታን ያለመቀበል ሀሳብም አለበት። ግን ዋናው ሃሳቡ ትንሳኤ ነው። የሰው ልጅ በጣም የሚወደውን፣ የሚያፈቅረውን ሰው ድንገት በሞት ሊያጣ ይችላል። ከዚያ ምንድነው የሚሆነው? ምንድነው መሰለህ? ‘በጣም የምትወደውን ሰው ህልም በመኖር ሰውየውን ማኖር ትችላለህ። ዕድሜ ልክ ሊኖሩ ይችላሉ የሚል ሀሳብ ያለው ሀሳብ ስለሆነ ትንሽ ጥልቅ ፊልም ነው። አንድ ሰው ከሁለት አሻንጉሊቶች ጋር የሚጫወተው ፊልም ነው። እና ትልቁ ተግዳሮት የነበረው አንድን ተዋናይ ከሁለት አሻንጉሊት ጋር ሙሉ ሰዓት ከተመልካች ጋር መግባባት ፈጥሮ እንዲቆይ ማድረጉ ነው።

ሌላ«ዓለሜ»ላይ ትልቅ ሙከራ ያደረግኹት የፊልም ሥራውን ነው። ፊልም ሥራው አሁንም በጣም የምኮራበት ነው። በ5D ነው የተቀረጸው፣ ካሜራው ትንሽ ፎርማት ነው ግን በጣም ኃይለኛ Computer Generated Images (CGI) የሚሠራ ዳንኤል ታምራት የሚባል ልጅ እና ሌላኛው Production Designer ተስፋዬ ወንድማገኘሁ የሁለቱ ግብዓት ፊልሙን ለምናቤ የቀረበ አድርጎታል። እኔ በምናቤ የምስለውን ነገር ቀርጬ አላውቅም እላለሁ።«ዓለሜ» ግን ለምናቤ የቀረበ ፊልም ነው። ያሰብኩትን ነገር በትክክል ለማሳካት የተጠጋሁበት ነበር። በእነዚህ ሁለት ልጆች እገዛ ወደዚያ፣ ወደ ህልሜ ቀርቧል ብዬ አምናለሁ ይላል ሰውመሆን።

የወጣቱ ፊልም ሰሪ ሥራ ከአገር ተሻግሮ ዓለም አቀፍ እውቅና ያገኘው በቅርቡ በሠራው «እውር አሞራ ቀላቢ» በተሰኘው ፊልሙ ነው። ዘካሪያስ ጥበቡ በተባለ ኢትዮጵያዊ የስደት እውነተኛ ታሪክ ላይ ተመስርቶ የተሠራው ይህ ፊልም በፌስቲቫሎች ሽልማቶች እና እውቅናዎች አግኝቷል። ባለፈው ግንቦት በተካሄደው የኒውዮርክ አፍሪካ ፊልም ፌስቲቫል ላይ የፌስቲቫሉ ዋና ፊልም ሆኖ ተመርጧል። በዳላስ ኢንተርናሽናል አፍሪካ ፊልም ፌስቲቫል ላይ ደግሞ ሽልማት አግኝቷል።

ከአዲ ዳዕሮ-አዲግራት እስከ ገላባት ሱዳን፣ ከመተማ እስከ ጅቡቲ ድንበር፣ ከአፋር እስከ ትግራይ፣ ከአዲስ አበባ እስከ ጎንደር ተዘዋውሮ የተቀረጸው ይህ ፊልም በመጪው መስከረም ወር በኢትዮጵያ መታየት ይጀምራል ተብሏል። ወጣቱ የፊልም ባለሙያ በዚህኛው ፊልም ከሙከራዎች አልተገታም።በ«እውር አሞራ ቀላቢ»ም በተወሰነ መልኩ ሙከራ አድርገናል ብዬ አምናለሁ። የዶክመንተሪ ድራማ ይዘት ያለው ሥራ ነው። ምን ማለት ነው? እውነተኛ ድርጊቶቹን እንደገና መልሰን ሠርተናል። ተዋንያን ስንመርጥም በሕይወት የሌሉትን ሰዎች ብቻ ነው ተተኪ ተዋናይ ያደረግነው።

በሕይወት ያሉትን ራሳቸው ባለታሪኮቹን ታሪኩ የተፈጸመበት ቦታ ድረስ እየሄድን ነው የቀረጽነው። ዋናው ታሪክ ከስደት በኋላ ቤተሰቦቹን፣ አጎቱን እና የአጎቱን ልጆች ለማግኘት ስለሚመጣ ልጅ ነው። ወደ አጎቱ ልጆች ቤት የሚሄደውም በእውን ነው የቀረጽነው። ሲገናኙ፣ እናቱ እና አባቱ መቃብር ሄዶ የሚያይበት፣ ለቅሶ የሚደርስበት ገቢሮች አሉ። እነርሱ የእውነት ነው የተቀረጹት። ከእዚያ ደግሞ ከእርሱ ተነስተን ጉዞውን፣ የተሰደደውን፣ የሄደውን መንገድ፣ የተሰቃየውን ስቃይ እርሱን ደግሞ በድራማ አድርገን ነው የሠራነው። ሁለቱን ቀላቅለን ነው ፊልም ያደረግነው።

«ይሄኛው ሌላ ዓይነት መንገድ ነው» ይላል ሽልማት ስላጎናፈው ፊልም ለየት ያለ ዘውግ ሲያብራራ።«ከፊልም ፊልም እየተማርኩ ነው» የሚለው ሰውመሆን የሁለት ቀጣይ ሥራዎችን ቀረጻ አጠናቅቋል። ባህር ዳር ላይ የተቀረጸው አንደኛው ፊልሙ በተለይ እስከዛሬ ከሠራኋቸው ሁሉ ሃሳቦቼን በደንብ የገለጽኩበት ነው ይላል። በፊልም ሥራ ስለሚከተለው ፍልስፍና ሲጠየቅ በረጅሙ ተነፍሶ፣ የፊልም ባለሙያው ፕሮፌሰር ኃይሌ ገሪማ ከዚህ ቀደም የተናገሩትን አጣቅሶ ተከታዩን ምላሽ ይሰጣል።

ፍልስፍና ይሁን፣ ምን ይሁን አላውቅም ብቻ ጋሽ ኃይሌ በጣም ደጋግሞ «የሰው ልጅ በጣም የሚውቀውን ነገር መሥራት አለበት»ይላል። እኔም ደጋግሜ ስሰማው በጣም እየገባኝ የመጣው ነገር እርሱ ነው። በጣም የምታውቀውን ነገር ስትሠራ ኃይለኛ ይሆናል። ዓለም ላይ በደንብ መታየት እንችላለን ብዬ አስባለሁ። በደንብም የሰው ልጅ የሚያውቀውን ነገር መሥራት አለበት። በጣም ብዙ ነገር አለን። አንዳንድ ልጆች ይመጣሉ የፊልም ጽሑፍ ይዘው ይመጣሉ። የሆነውን ገቢር ስታነበው የሆነ ፊልም ይመስልሃል፣ ሌላኛውን ገቢር ስታነበው ሌላ ፊልም ይመስልሃል።

ከዚያ እስኪ የእናትህን ታሪክ ንገረኝ፣ እናትህ እንዴት ናቸው?፣ አባትህ እና እናትህ እንዴት ተገናኙ ስትለው ጉደኛ ታሪክ ይነግርሃል። እና ምን ሆነ ነው ከዚህ ጋር የምትላፋው፣ ምን ይሠራልሃል ይሄ፣ የምትነግረኝ ነገር እኮ በጣም የሚገርም ነው ስትለው አፉን ይዞ ልጁ ተመልሶ ይሄዳል። ስለዚህ በትክክል የሰው ልጅ የሚያውቀውን ነገር መሥራት አለበት ብዬ አምናለሁ።

ይሄ ነው ለእኔ ሲኒማ ውስጥ ያለኝ ሀሳብ። እና የእውነት መነሳሳት ያስፈልገዋል። በቃ! ከነፍስህ፣ ከልብህ ጋር ሲገናኝ ታገኘዋለህ። የእውነት ከውስጥህ ሲወጣ ነው በትክክል የሚሠራው ብዬ አምናለሁ ሲል እምነቱን ለጀርመኑ ዶቼ ቬለ ጋዜጠኞች ተስፋለም ወልደየስ እና ሸዋዬ ለገሠ ይገልጻል። እኔም ሰውመሆንንም ሆነ ቡድኑን ወይም ከሩው «ፍቅር እስከ መቃብር»ን ወደ ፊልም ለመቀየር ሥራ ሲጀምር ይህን ዘመንና ትውልድ ተሻጋሪ ሥራ በደንብ ጥንቅቅና ልቅም አድርጎ አውቆ ይሆናል ብዬ በጽኑ አምናለሁ።

ሻሎም ! አሜን×፫።

# ወቅታዊ

# “በሁለት አመታት ውስጥ 10 ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ ይሆናሉ”

ዶክተር ሰለሞን አብርሃ
በትምህርት ሚኒስቴር የአስተዳደርና መሰረተ ልማት ዋና ስራ አስፈጻሚ

እፀገነት አክሊሉ

ትምህርት ሚኒስቴር በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ 10 የመንግስት ዩኒቨርሲቲዎችን ራስ ገዝ ለማድረግ እቅድ ይዟል። በዚህ እቅድ ውስጥ ከተካተቱት መካከልም ፤ ባህርዳር፣ ጎንደር፣ ጅማ፣ ሀዋሳ፣ አርባ ምንጭ እና መቐለ ዩኒቨርሲቲዎች ይገኙበታል። ከተቋቋመ ሰባ ሁለተኛ ዓመቱን የያዘው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ በተያዘው በጀት ዓመት የ“ራስ ገዝ” አስተዳደርን ተግባራዊ በማድረግ የመጀመሪያው ይሆናል ተብሎ ይጠበቃል።

የዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ መሆን በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአጭር ጊዜ ውስጥ መዋቅራዊ ሽግግር ለማምጣት እንደሚያስችል የትምህርት ሚኒስትር በተደጋጋሚ እየገለጸም ይገኛል። የዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ መሆን መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣትና ከሚታወቀው በተሻለና በተለየ መልኩ በአጭር ጊዜ ውስጥ መዋቅራዊ ሽግግር እንዲመጣ ወሳኝነት እንዳለውም ይታሰባል።

ዩኒቨርሲቲዎች ተልዕኮአቸው ላይ ብቻ ትኩረት እንዲያደርጉ፣ ተወዳዳሪና ብቁ ችሎታ ያላቸው ምሩቃንን ለማፍራትና ጥራት ያለው የምርምር ውጤት እንዲሰሩ በማድረጉ በኩልም ራስ ገዝነታቸው ይጠቅማቸዋል ተብሏል።

ዩኒቨርሲቲዎች ችግር የሚያባብሱ ሳይሆን በሰላም መኖርን፣ ዴሞክራሲን፣ የሚሰብኩ ተቋማት እንዲሆኑ በተለይ አገር በቀል እውቀቶችን በምርምር ማወቅ፣ ለችግሮች የመፍትሄ ሃሳብ ማመንጨት፣ የዓለምንና የአገሪቱን ነባራዊ ሁኔታ በመረዳት ቀጣይ አቅጣጫን ለማመላከትም ነጻነትና ራስ ገዝነት እንደሚያስፈልግ ታምኖበታል።

ይህንን ለማረጋገጥ በመንግሥት ቁርጠኝነት ዩኒቨርሲቲዎች ወደ ራስ ገዝነት እንዲሸጋገሩ በተወሰነው መሰረት የተለያዩ እንቅስቃሴዎች መጀመራቸው ይታወቃል። በዚህም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ዩኒቨርሲቲዎችን የራስ ገዝ የማድረግ ረቂቅ አዋጅን መርምሮ እና አጽድቆ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም አስተላልፏል።

እኛም ራስ ገዝነት ለዩኒቨርሲቲዎች ብሎም ለማህበረሰቡ አልፎም ለተማሪው እንደ አገርም በትምህርት ጥራቱ ላይ ሊያመጣ ስለሚችለው ለውጥ በትምህርት ሚኒስቴር የአስተዳደርና መሰረተ ልማት ዋና ስራ አስፈጻሚ ከሆኑት ከዶክተር ሰለሞን አብርሃ ጋር ቆይታን አድርገናል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ ይሆናሉ ማለት ምን ማለት ነው?**

**ዶክተር ሰለሞን፡-** ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝነት ወይም በሌላ ስሙ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተቋማዊ ነጻነት ማለት ተቋማቱ የአስተዳደራዊ፤ የአካዳሚክ፤ የምርመር፤ የሰው ሃብት አስተዳደር፤ የፋይናንስ ጉዳዮቻቸውን ነጻነት ኖሯቸው በዛው ልክ ደግሞ ተጠያቂነትም እንዳለባቸው አውቀው የሚተገብሩበት ሥርዓት ነው፡፡

አንድ ተቋም ተቋማዊ ነጻነት ተጎናጽፏል ወይም ራስ ገዝ ሆኗል ብለን ስናስብ በዋናነት ከአካዳሚና አስተዳደራዊ ጉዳዮች ጋር ተያይዞ ነጻነት ኖሯቸው ይህንንም ከተጠያቂነት ጋር በመያዝ የተሻለና ውጤታማ ስራን እንዲሰሩ የማስቻል ጅምር ነው፡፡

አስተዳደራዊ ነጻነቱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ የራሳቸውን አደረጃጀት እና መዋቅር የመዘርጋት ስልጣን ይሰጣቸዋል፤ በዚህ መሰረት ዩኒቨርሲቲዎቹ ከፍተኛ አመራሮቻቸውን ጨምሮ በመዋቅራቸው ውስጥ የሚያስፈልጓቸውን የአመራር እና የአስተዳደር አካላትን በራሳቸው መመደብ እንደሚችሉ መንገድ ይከፍትላቸዋል፡፡

በሌላ በኩልም ፋይናንሻል አቅማቸውን በጀታቸውን በአግባቡ የመጠቀም እድል ይፈጥርላቸዋል። ዩኒቨርሲቲዎች አመራሮችን የመሻር፤ የመሾም፤ ሀብት የመፍጠር ፤የውስጥ መመሪያዎችንና አስተዳደራዊ ስርዓቶችን የመዘርጋት ነጻነት ይኖራቸዋል። ከሁሉም በላይ ደግሞ የሰው ሀብታቸውን በአግባቡ ከመጠቀም


ፎቶ - አጋፔ ጊዮን

**በተቋማቱ ላይ የሚደረገው የመንግስት ኢንቨስትመንት ይቀጥላል። ግን ደግሞ ዩኒቨርሲቲዎቹ ከተልኳቸው ጋር በተያያዘ ሀብት እንዲያመነጩ ይጠበቃል። ይህ ማለት ደግሞ ገንዘብ ማመንጨት ሲችሉ ወጪዎቻቸውንም መሸፈን ይጀምራሉ ማለት ነው**

ብሎም ብቃት ያላቸውን ባለሙያዎች የመቅጠርና ሥርዓቱን እንዲሁም ደመወዝና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን የመወሰን አቅም ይፈጥርላቸዋል። በተለይም ለዩኒቨርሲቲው ብሎም ለአገር ይጠቅማል፡፡ ችግር ፈቺ የምርምር ስራዎችን ይሰራል ብለው ያመኑበትን ባለሙያ በድርድር እስከ መቅጠር ድረስ የሚደርስ ነጻነት እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል፡፡

ከተማሪዎች ቅበላ ጀምሮ አስመርቆ እስከማውጣት ድረስ ያለው ሂደት ጤናማ ብሎም በእውቀት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ለማድረግ ተማሪዎችን አወዳድሮ እስከመቀበል ድረስ ያለውን ውሳኔ የማንንም ድጋፍ ሳይጠይቁ የመወሰን አቅም ይፈጥርላቸዋል፡፡

ተቋማት ራስ ገዝ በሆኑ ቁጥር ለሚያስተምሯቸው ተማሪዎች ምን ዓይነት የትምህርት ሥርዓት መከተል እንዳለባቸው ገበያውም በሚፈልገው ልክ የመወሰን ከዛም አልፎ የሚያስትምሩበትን ቋንቋም እስከ መወሰን ድረስ እድል ይኖራቸዋል፡፡

**አዲስ ዘመን ፡-ከዚህ ቀደም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማቱ በቦርድ ይተዳደሩ ነበር፡፡ በዛም አንዳንድ ጉዳዮቻቸውን በቦርድ የማስወሰን አካሄድም እንደሚከተሉ ይታወቃል ፤ አሁን ራስ ገዝ መሆናቸው ምን ይጨምርላቸዋል?**

**ዶክተር ሰለሞን፡-** ልዩነቱ ዩኒቨርሲቲዎች የመንግስት ተቋማት በመሆናቸው በጀታቸውንም ሙሉ በሙሉ የሚያገኙት ከመንግስት ነው፤ በቦርድ ይተዳደሩ እንጂ የራሳቸው የሆነ የፋይናንስ የሰው ሃብት የግዢ አስተዳደር አልነበራቸውም ። የሲቪል ሰርቪስ የሚወጣ የሰው ሃብት አስተዳደር ነው የሚከተሉት። በገንዘብ ሚኒስቴር የሚወጣ የግዢና የፋይናንስ ሥርዓትን ነው ሲከተሉ የኖሩት። ይህ ደግሞ አሁን ባለው ሁኔታ ብሎም ተቋማቱ ካላቸው ልዩ ባህርይ አንጻር ምቹ ሆኖ አልተገኘም። ምቹ አለመሆን ብቻ ሳይሆን ተቋማቱ ለቆሙለት የትምህርት ጥራት የማረጋገጥ ስራ እንቅፋት ፈጥሯል። በመሆኑም ተቋማቱ ተቋማዊ ነጻነትን ተጎናጸፉ ስንል የራሳቸው የሆነ የፋይናንስ የግዢ ሥርዓት እንዲኖራቸው እድል ሰጥቷል ማለት ነው። አዋጁም ጸድቋል። በመሆኑም ከዚህ በኋላ ወደራስ ገዝ የሚመጡት ተቋማት የራሳቸው የሆነ በቦርድ የሚጸድቅ የፋይናንስ የግዢ የሰው ሃብት አስተዳደር ይኖራቸዋል። ይህ ደግሞ እንደ ተቋም ትልቅ ነጻነትን የሚፈጥር ነው።

ተቋማቱ ተማሪን አስተምረው ያስመርቃሉ፤ የምርምር ስራን ይሰራሉ፤ ብዙ ዓይነት ውስብስብ ስራዎችን በኃላፊነት ይሰራሉ፤ ከዚህ አንጻር አሁን ያለው የግዢ የፋይናንስ ስርዓት ውጤታማ እንዲሆኑ አላስቻላቸውም። በመሆኑም ተቋማቱ ራስ ገዝ ሲሆኑ ብዙ ነገሮች ስለሚቀሉላቸው በዛው ልክ ውጤታማም የሚሆኑበት እድል የሰፋ ይሆናል።

በጠቅላላው ከዚህ በኋላም በቦርድ የሚመሩ ቢሆኑም ቦርዱ ትልቅ ስልጣንና ኃላፊነት የሚሰጠው አቅምና ብቃት ያላቸውን ሰዎች የሚያካትት ይሆናል፡፡

**አዲስ ዘመን ፡- ተቋማት ራስ ገዝ በመሆናቸው ብዙ ነገሮቻቸውን በራሳቸው የመወሰን እድልን አግኝተዋል ፤ ነገር ግን ከፍ ያለ ነጻነት ለብልሹ አሰራር ብሎም በአገር ደረጃ ወጥ የሆነ አካሄድ እንዳይኖርስ አያደርግም በዚህ ላይ ምን ታስቦበታል ?**

**ዶክተር ሰለሞን፡-** ተቋማቱ አሁንም የመንግስት ተቋማት ናቸው። የመንግስት ዩኒቨርሲቲ መሆናቸው ይቀጥላል። በዚህም የመንግስት ተጠያቂነቱም ይቀጥላል ማለት ነው። ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ራስ ገዝ የሚለው ሥርዓት ነፃነትን ከተጠያቂነት ጋር የሚሰጥ እንጂ ነጻነትን ብቻ ሰጥቶ ልቅ የሚያደርግ አይደለም፡፡

በመሆኑም አደረጃጀቱ በግልጽ ይቀመጣል፤ ሕጎችና ሥርዓቶች ይኖራሉ፤ በእነዚህ ሕግና ሥርዓቶች የሚመራ እንጂ የግል ተቋም አይደለም፤ ቀጣይም የሕዝብ ተቋም ናቸው፤ ይህንን መገንዘብ ያስፈልጋል። በመሆኑም ለእያንዳንዱ ውሳኔ ተጠያቂነት እንዳለው ማወቅ ያስፈልጋል። ለምሳሌ ግዢ በቦርድ ጸድቆ ይፈጸማል ማለት ተጠያቂነት በሌለው ሁኔታ ልቅ ይተዋል ማለት አይደለም። ሌላውም እንደዛው ነው። በመሆኑም ነጻነቱ በዛ ብሎ መሰጠቱ ለአሰራር እንዲያመች፤ ሰበባ ሰበቦች እንዳይበዙ የሚያደርግ እና የምንፈልገውም የትምህርት ሥርዓት አሳሪ በሆኑ የተንዛዙ አሰራሮች እንዳይጠለፍ ለማድረግ እንጂ አሰራሮች ልቅ እንዲወጡ አለመሆኑ መታወቅ ይኖርበታል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- እነዚህ ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ ሆነው የራሳቸውን ገቢ የሚያመነጩ ከሆነ ከግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በምን ይለያሉ?**

**ዶክተር ሰለሞን ፡-** በተቋማቱ ላይ የሚደረገው የመንግስት ኢንቨስትመንት ይቀጥላል። ግን ደግሞ ዩኒቨርሲቲዎቹ ከተልኳቸው ጋር በተያያዘ ሀብት እንዲያመነጩ ይጠበቃል። ይህ ማለት ደግሞ ገንዘብ ማመንጨት ሲችሉ ወጪዎቻቸውንም መሸፈን ይጀምራሉ ማለት ነው። በመሆኑም ተቋማቱ የሕዝብ ተቋማት መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ተማሪዎችን እያስከፈሉ ትምህርት መስጠታቸው አንዱ የገቢ ምንጫቸው ነው። በዓለም አቀፍ ያሉ ትልልቅ ዩኒቨርሲቲዎችም ከመንግስት የሚደረግላቸው ድጎማ እንዳለ ሆኖ ከተማሪ የሚያገኙት ክፍያ እንዲሁም የተለያዩ ምርምሮችን በማድረግ የሚያገኟቸው ሀብቶች ስራዎቻቸውን ይደጉማሉ፡፡

ሀብት ያመነጫሉ ሲባል ግን ቀጥታ የንግድ ሥርዓት ውስጥ ገብተው ከነጋዴ ጋር ይወዳደራሉ ማለት አይደለም። ከሚሰጣቸው ተልዕኮ አንጻር ነው የሚሰሩት፤ ለምሳሌ ከሚሰጧቸው ተልዕኮዎች አንዱ የመማር ማስተማር ስራ ነው፤ ሲያስተምሩ ገንዘብ ያገኛሉ በሌላ በኩል ደግሞ የምርምር ስራዎችን ያከናውናሉ ይህንን ሲያደርጉ ገንዘብ ያገኛሉ። የማህበረሰብ አገልግሎት ሲሰጡ ሲያማክሩ ገንዘብ ያገኛሉ፤ ይህ ደግሞ ሀብት የማመንጨት ሂደቱ ነው። ያመነጩትን ሀብት ደግሞ ለትምህርት ጥራት ለምርምር ሥራ ያውሉታል ማለት ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ሌላው በተቋማቱ ራስ ገዝ መሆን ላይ የሚነሳው ነገር የፍትሐዊነት ነው፤ መክፈል የሚችል ብቻ የሚማርባቸው ተቋማት እንዳይሆኑስ የታሰበው ምንድን ነው?**

**ዶክተር ሰለሞን፡-** ተቋማቱ የመንግስት

# ወቅታዊ

# “በሁለት አመታት...



ከገጽ 7 የዞረ

እንደመሆናቸው መጠን ሥራቸው ፍትሃዊነትን የማረጋገጥ ሥራ ነው። አንድ ተቋም ራስ ገዝ ሲሆን ተማሪን ፈትኖ ባስቀመጠው መስፈርት መሰረት ይቀበላል። በዚህም ተማሪዎች ሲገቡ ተወዳድረው አቅም ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፤ ግን እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነገር አቅሙ ኖሮት ደግሞ ከፍሎ መማር የማይችለውን ተማሪ የማስተማር ጉዳይ የመንግስት ኃላፊነት ይሆናል። መንግስት ይህንን ኃላፊነት ወስዶ ተማሪዎቹ ነጻ የትምህርት እድልን የሚያገኙበትን ሁኔታ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመሆን ይሰራል።

በመሆኑም አቅም ኖሮት መክፈል የሚችል ይከፍላል፤ መስፈርቱን አሟልቶ የመክፈል አቅም የሚያንሰውን ደግሞ መንግስት ኃላፊነቱን ወስዶ ያስተምራል፡፡በመሆኑም ተቋማቱ ራስ ገዝ ሆኑ ማለት ወደግል ተቋምነት ተቀየሩ ማለት አይደለም። ተደራሽነታቸውን የማረጋገጡ ስራ እንዳለ ሆኖ ፍትሀዊነትንም የማረጋገጥ ስራው በዛው ልክ ይሰራል፡፡

**አዲስ ዘመን፦ የራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲዎች የሌሎች አገራት ተሞክሮ ምን ይመስላል?**

**ዶክተር ሰለሞን ፦** በነገራችን ላይ ዩኒቨርሲቲዎችን ራስ ገዝ የማድረግ ጅምሩ ቀደም ባለው ጊዜ በእኛም አገር የነበረ ነው። አሁን ባለንበት ዘመን በጣም ትልልቅና ብዙ የምርምር የቴክኖሎጂ ሽግግርን እያደረጉ ያሉ በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ የሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ የሆኑ ናቸው። ምክንያቱ ደግሞ የትምህርት ስራ በራሱ ከፍ ያለ ነጻነትን የሚፈልግ ነው። ለምሳሌ ምርምር ሲካሄድ የተለያዩ ግብዓቶች ያስፈልጋሉ፤ ግብዓቶቹ ደግሞ በአስቸኳይ የግዢ ሥርዓት መፈጸም ሊኖርባቸው ይችላል። ነገር ግን አሁን ያለው የፋይናንስና የግዢ ሥርዓት ይህንን የሚፈቅድ አይደለም ። በመሆኑም እነዚህ ችግሮች ተቀርፈው ዩኒቨርሲቲዎች ችግር ፈቺ ሊሆኑ የሚችሉት ራሳቸውን ማስተዳደር ሲችሉ ብቻ ነው። ዛሬ ላይ ቆመን በዓለም አቀፍ ደረጃ ልንጠራቸው የምንችላቸው ስመ ጥር ዩኒቨርሲቲዎችም ራስ ገዝ ናቸው። የውጤታማነታቸው ምስጢርም ይኸው ነው።

ለምሳሌ እነ ሀርቫርድን ጨምሮ የስቴት ዩኒቨርሲቲዎች የመንግስት ናቸው። ግን ደግሞ ራስ ገዝ አስተዳደርን ስለሚከተሉ በዩኒቨርሲቲዎች ደረጃ ላይ ሁሌም ከላይ የሚታዩ ናቸው። በመሆኑም ራስ ገዝ ማድረግ የዓለም ተሞክሮም እንደሚያሳየው በትምህርት ጥራት ፤ በምርምር ስራዎች ላይ የራሱ የሆነ አዎንታዊ ሚና እንዳለው ነው።

እኛም ከመሬት ተነስተን አይደለም ዩኒቨርሲቲዎቻችን ራስ ገዝ ሊሆኑ ይገባል በማለት ወደ ስራ ይገባነው። ባለፉት ሁለት አስርተ ዓመታት በትምህርት ተደራሽነት ላይ ከፍ ያለ ሥራ ተሰርቷል፤ አሁን በመንግስት ደረጃ 51 ዩኒቨርሲቲዎች አሉን ፤ በግል 5 እንዲሁም 325 አካባቢ የግል ኮሌጆችም አሉን። በመሆኑም ይህ ተደራሽነት ጥሩ ቢሆንም የዛሬ አምስት ዓመት የትምህርት ፍኖተ ካርታ ጥናት ሲካሄድ የተገኘው ውጤት የሚያሳየው ተደራሽነቱ አበረታች ቢሆንም የትምህርት ጥራቱ ላይ ግን ችግር እንዳለ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘም ምን መሰራት አለበት ለሚለው ፍኖተ ካርታው ካስቀመጠው ምክረ ሃሳብ አንዱ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ራስ ገዝ ማድረግ ነው፡

በመሆኑም የዚህን የጥናት ውጤት በመያዝ ዩኒቨርሲቲዎቹ ራስ ገዝ የሚሆኑበትን አሰራር የማመቻቸት ሂደት ነው የተጀመረው። ራስ ገዝ የመሆን ጉዳይም ከጥናቱ ጋር አብሮ የመጣ ጉዳይ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

የዓለም ተሞክሮ የሚያሳየንም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ነጻነት ለአካዳሚክ ውጤታማነት ጉልህ ሚና እንዳለው ነው። ሌላውና የሚገርመው ነገር ራስ ገዝ በአገራችን ዛሬ የተጀመረ አሰራር አይደለም ፤ በንጉሱ ጊዜ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ሲቋቋም ራስ ገዝ ሆኖ ነው የተቋቋመው ፤ በዛን ወቅት የነበረውን ተሞክሮም መለስ ብለን ስናየው በትምህርት ጥራት ላይ የነበረው ሚና ቀላል የሚባል አልነበረም ፤ ሆኖም ከመንግስት ለውጥ ጋር በተያያዘ በዛ መልኩ መቀጠል ባለመቻሉ አሁን የደረስንበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። በጠቅላላው ግን ራስ ገዝ አንዱ የትምህርት ሚኒስቴር የሪፎርም ስራ አካል ነው፡፡

ከራስ ገዝነት በተጓዳኝ ጥናቱን መሰረት በማድረግ ዩኒቨርሲቲዎችን በሚና የመከፋፈል ሥራ ይሰራል። አሁን ላይ ዩኒቨርሲቲዎቻችን በሙሉ የሚሰጡት ትምህርትም ሆነ ደረጃቸው ተመሳሳይ ነው፤ ነገር ግን አንድ ዓይነት መሆን አይጠበቅባቸውም ። ስለዚህ ዩኒቨርሲቲዎቹ በትኩረትና በተልዕኮ ሊለያዩ ይገባል፤ ይህም ሲባል የተወሰኑት ምርመር ሌሎቹ አፕላይድ ሳይንስ የተቀሩት ህክምና ከዚህ የሚተርፉት ደግሞ የመማር ማስተማር ሥራውን ከምርመሩ ጋር አዋህደው ይቀጥሉ ተብሎ ዩኒቨርሲቲዎቹን የመለየት እንዲሁም ካላቸው አካባቢያዊ ሁኔታና ጸጋ እንዲሁም ከኋላ ታሪካቸው በመነሳት ትኩረት እንዲያገኙ ሆኗል። በዚህ መነሻነትም ከዚህ በኋላ ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ተመሳሳይ ሥራን አይሰሩም፡፡

**አዲስ ዘመን፦ አሁን ላይ የራስ ገዝ የመሆን ጉዞውን እንዲጀምር አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መመረጡ ተነግሯል ሌሎቹስ መቼ ነው የሚገቡት?**

**ዶክተር ሰለሞን፦** አሁን ባለው ሁኔታ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ካለው ልምድ ከእድሜውና ከሌሎች ነገሮች አንጻር ተመራጭ ሆኗል። በነገራችን ላይ አዋጁ አንድ ተቋም ምን ሲያሟላ ራስ ገዝ እንደሚሆን በግልጽ አስቀምጧል፤ ከዚህም ውስጥ ያለው ታሪካዊ ዳራ ፡፡ አቅሙ የሰራተኞች ብዛትና የስራ ዘርፍ ፡፡ ዩኒቨርሲቲው ራስ ገዝ ቢሆን ራሱን የማስተዳደር አቅሙ ምን ያህል ነው? የሚሉት ነገሮች ሁሉ ታይቶ ነው የሚመረጠው። በዚህ መስፈርት መሰረት አሟልቶ የተገኘው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ነው። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ የመጀመሪያው ትውልድ ዩኒቨርሲቲ የምንላቸው ስምንት ያህል ተቋማት ወደ ራስ ገዝነት ይገባሉ። ቀስ በቀስም ዩኒቨርሲቲዎች አቅማቸው እየታየ ወደ መስመር ይገባሉ። ነገር ግን በሁለት አመት ውስጥ አስር ዩኒቨርሲቲዎች ሙሉ በሙሉ ራስ ገዝ ሆነው ይወጣሉ፡፡

**አዲስ ዘመን ፦ ዘንድሮ የሚጀመረው የተማሪዎች የመውጫ ፈተና ዝግጅት ምን ደረጃ ላይ ይገኛል ?**

**ዶክተር ሰለሞን ፦** 280 ሺ ለሚሆኑ ተማሪዎች ፈተናውን ለመስጠት ዩኒቨርሲቲዎቹ ከፍ ያለ ዝግጅትን እያደረጉ ነው። ከሐምሌ 3 እስከ 8 ቀን 2015 ዓም ደግሞ ፈተናው ይሰጣል። በዚህ ዓመት የሚመረቅ ተማሪ ሁሉ የመውጫ ፈተናውን ይወስዳል ማለት ነው፡፡

ተማሪን ፈትኖ ማስገባት ብሎም የተማረውን ምን ያህል አውቋል ብሎ ደግሞ መጨረሻ ላይ ፈትኖ ማስወጣት እኛ አገር አሁን ይጀመር እንጂ ሌሎች አለማት ይሰሩበታል። ዋናው ዓላማውም ተማሪዎች የሚፈለግባቸውን ወይም ሊያውቋቸው የሚገቡ መሰረታዊ እውቀቶች ይዘዋል ወይ? የሚለውን መለካት ነው። ተማሪዎች ሶስትም አራትም አምስትም ከዛ በላይም አመት በትምህርት ያሳልፉ መጨረሻው ግን በተማሩት ትምህርት በኩል ያሉትን መሰረታዊ ነገሮች ያውቃሉ ወይ የሚለውን የምንለካበት ነው። ተማሩ በዚህ ሥርዓት ውስጥ ሲያልፍና እውቀቱ ተመዝኖ ሲታይ በትምህርት ጥራት ላይ የሚኖረው አዎንታዊ ተጽዕኖ ቀላል የሚባል አይደለም፡፡

ለምሳሌ አንድ ሰው በአንድ ሙያ ተምሮ ሲወጣ ስለተማረው ትምህርት ጽንሰ ሃሳብ ምንድነው? የሚለውን ነገር ከማወቅ ጀምሮ የዛ ሙያ ባለቤት ነው ሊያስብለው የሚችለውን ነገር አውቋል ወይ? የሚለው ሲለካና ሲረጋገጥ ያኔ ወረደ ስለምንለው የትምህርት ጥራትም ተጨባጭ መረጃን እንይዛለን ማለት ነው፡

በጠቅላላው አንድ ተማሪ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ገብቶ ሲማር ከእውቀት፤ ከብቃት፤ ከክህሎት አንጻር አውቋቸው እንዲወጣ የሚፈለጉ ነገሮች አሉ፤ እነዚህን ነገሮች በሚገባ ጨበጠ ማለት ደግሞ ኢንደስትሪው ላይ ሲገባ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ በኩል የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል ማለት ነው፡፡

በመሆኑም የመውጪያ ፈተናው ጠቅለል ያለ ተማሪዎች በተማሩት ሙያ ዘርፍ ላይ ዋና ዋና የሚባሉ ጉዳዮችን አውቀዋል ወይ ?እውቀቶችን ጨብጠዋል ወይ? የሚለውን የሚለካበት ሥርዓት ከመሆኑ አንጻር ለትምህርት ጥራቱም የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ነው።

**አዲስ ዘመን፦ ሌላው እንግዲህ ዶክተር በትግራይ ክልል የትምህህርት ዘርፉን ወደነበረበት ስመመለስ የተለያዩ ጥረቶች ነበሩና አሁን ላይ ምን ውጤት አለ ?**

**ዶክተር ሰለሞን፦** የፕሪቶሪያውን ሰላም ስምምነት መሰረት ጦርነቱ ቆሟል። የሰላም አንዱ መገለጫው ደግሞ ትምህርት በመሆኑ በተለይም ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወደሥራ መግባታቸው አንዱ ለሰላም ስምምነቱ ተፈጻሚነት ማሳያ በመሆኑ እንደ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ስምምነቱ ከተፈረመ በኋላ ወዲያውኑ ኮሚቴ አዋቅረን መቀሌ በመሄድና የአራቱንም ዩኒቨርሲቲዎች አመራሮች በመጠራት ያሉበትን ሁኔታ፤ የደረሰባቸውን ጉዳትና ሊደረግ በሚገባውን ነገር ዙሪያ ውይይት አድርገናል፤ እነሱም አለ ስለሚሉት ነገር ሪፖርት አቅርበውልን አይተናል፡፡

እንደ ትምህርት ሚኒስቴርም አክሱም ዩኒቨርሲቲ ከፍተኛ ጉዳት ደርሶበታል የሚል መረጃ ስለነበረን በቦታው ላይ ቅኝት የሚያደርግ ቡድን በመላክና ሁለት ሳምንት እንዲቆዩ በማድረግ የትምህርት ክፍሎቹን አዲሱ አመራር እንዲረከበው የማድረግና የጽዳት ስራዎች ተሰርተው ወደ ስራ እንዲመለስ የማድረግ ተግባር ተከናውኗል፡

በአሁኑ ወቅትም ዩኒቨርሲቲዎቹ ተማሪዎችን ለመቀበል የሚያስችላቸው ቁመና ላይ እየደረሱ ነው። በእኛ አገር ተጨባጭ ሁኔታ ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲ ሲገቡ ምግባቸውም ማደሪያቸው እንዲሁም የጤና ሁኔታቸው ሁሉ ክትትል የሚደረገው በመንግስትና በተቋማቱ በመሆኑም በእነዚህ ዩኒቨርሲቲዎችም ተማሪዎች ሲገቡ እነዚህ ነገሮች ተሟልተው ሊጠብቋቸው ስለሚገባ ባለፉት ወራቶች ከትምህርት ሚኒስቴር እንዲሁም ከአካባቢው አመራሮች ጋር በመሆን እየተሰራ ያለው ይህ ነው፡፡

ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎችን ተቀብለው ለማስተማር የሚያስችላቸው ቁመና ላይ ናቸው ወይ መሰረተ ልማቱ ምን ይመስላል የሚለውን የማረጋገጥ ስራውም በዋናነት እየተሰራ ነው። በተወሰኑት ማለትም እንደ ራያ ዩኒቨርሲቲ ያሉትም ዝግጅታቸውን አጠናቀው ተማሪዎችን በመመዝገብ ላይ ናቸው፡፡

መከላከያ ትግራይን ለቆ በወጣበት ሰኔ ወር 2013 ዓ.ም ላይ በየዩኒቨርሲቲው ያሉ ተማሪዎችን ማስወጣት ነበረብንና በወቅቱ ከ20 ሺ በላይ ተማሪዎችን ከትግራይ አስወጥተናል። እነዚህን ተማሪዎችም በጊዜያዊነት በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ተመድበው ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉም ሆኗል። መመረቅ የነበረባቸውም ተመርቀዋል፤ የሚቀራቸውም እየተማሩ ነው። ነገር ግን ከትግራይ ያልወጡ የአካባቢው ተማሪዎች ቁጥራቸውም ከ20ሺ በላይ የሚሆነው እዛው አሉ። እነዚህን ተማሪዎች ሁለት ዓመት በጦርነቱ ምክንያት አልተማሩም በመሆኑም አሁን ላይ ትምህርታቸውን ካቆሙበት እንዲቀጥሉና ዩኒቨርሲቲዎቹ ደግሞ ዝግጁ ሲሆኑ የአዲስ ተማሪ ቅበላም የሚጀምሩበት ሁኔታ ታስቧል፡፡

አሁን ላይ ራያ ዩኒቨርሲቲ እዛ አካባቢ ያሉትንና ሌላ ቦታ ያልተመደቡትን ነባር ተማሪዎቹን ጠርቶ ምዝገባ እያደረገ ነው። መቀሌና አዲግራትም ከአንድ ወር በኋላ ወደ ስራ የሚገቡ ሲሆን አክሱም ዩኒቨርሲቲ የዛሬ ሁለት ወር ወደመማር ማስተማር ስራው ይገባል። ሁሉም ግን ለነባር ተማሪዎቻቸው ጥሪ ከማስተላለፍም በላይ ባሉበት ሆነው ምዝገባቸውን እንዲጨርሱም አድርገዋል። በዚህም ያላቸውን የተማሪ ቁጥርና ሊያደርጉ የሚገባቸውን ዝግጅት አውቀዋል፤ ጊዜው ሲደርስ ጠርተው ያስገባሉ።

በወቅቱ ተፈናቅለው የመጡ መምህራን በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ስራቸውን እንዲጀምሩ ተደርጓል። ነገር ግን አሁን ላይ ሁኔታዎች እየተስተካከሉ በመሆኑ ወደ ቀድሞ ዩኒቨርሲቲዎቻቸው ተመልሰው ሥራቸውን እንዲቀጥሉ ጥሪ እናደርጋለን፡፡

**አዲስ ዘመን፦ በመጨረሻም ማለት የሚፈልጉት ነገር ካለ?**

**ዶክተር ሰለሞን፦** አዎ እንግዲህ በተለይም ከተነሳንበት አንጻር ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ ይሆናሉ ወይም ይሁኑ ሲባል እንደ አገር ያለው ወይም የሚኖረው ፋይዳ በጣም ሰፊ ነው። በተለይም ብቁ የሰው ኃይል በማዘጋጀት ለአገራችን ኢንደስትሪዎች አቅም የሚጨምር ሥራ ያሰራል። ይህ ደግሞ ምርትና ምርታማነትን ያሳድጋል። ዩኒቨርሲቲዎች ራሳቸውን ችለው ብቃት ያለው መምህር ቀጠሩ ማለት ብቃት ያለው ተማሪን የማውጣት እድላቸውም ሰፋ ማለት ነው። በዛውም ብቃት ያለው ምርመር ይደረጋል፤ ቴክኖሎጂዎችም ይወለዳሉ። ማህበረሰቡም ተቋማቱ በዚህ አካሄድ የግል ተቋም ሊሆኑ ይችላሉ የሚለውንም ሃሳብ ማውጣት አለበት፡፡

**አዲስ ዘመን፦ ስነበረን ቆይታ በጣም አመሰግናለሁ፡፡**

**ዶክተር ሰለሞን፦** እኔም አመሰግናለሁ

**በነገራችን ላይ ዩኒቨርሲቲዎችን ራስ ገዝ የማድረግ ጅምሩ ቀደም ባለው ጊዜ በእኛም አገር የነበረ ነው። አሁን ባለንበት ዘመን በጣም ትልልቅና ብዙ የምርምር የቴክኖሎጂ ሽግግርን እያደረጉ ያሉ በዓለም አቀፍ ደረጃ ታዋቂ የሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች ራስ ገዝ የሆኑ ናቸው**

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግርን በአግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች

አንተነህ ቸሬ

የኢትዮጵያን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግርን እውን ለማድረግ አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል ተብለው ትኩረት ከተሰጣቸው ተግባራት መካከል የኢንዱስትሪ ፓርኮች (Industrial Parks) ልማት አንዱ ነው፡፡ የኢንዱስትሪ ፓርኮች የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የመሳብ፣ የሥራ ዕድል ፈጠራን የማስፋት እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን እውን የማድረግ ዋና ዋና መሠረታዊ ተልዕኮዎች አሏቸው። ፓርኮቹ በሚገነቡባቸው አካባቢዎች ለሚኖረው የኅብረተሰብ ክፍል ሥራ በመፍጠርና ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆነ የሥራ ከባቢ እውን በማድረግ ለአገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገት ትልቅ አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል፡፡

የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ተመራጭ ከሚያደርጓቸው ነገሮች መካከል በርካታ አገልግሎቶችን አንድ ሥፍራ ላይ ሰብሰብ አድርገው የሚያቀርቡ መሆናቸው፣ ተገቢ መሠረተ ልማት የሚገነባላቸው እንዲሁም ከሌሎች አምራቾች ጋርም የሚያገናኙ መሆናቸው ይጠቀሳሉ። ከዚህ አንፃር በኢትዮጵያ ብዙ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን በማቋቋም እንዲሁም በአንፃራዊነት ዝቅተኛ ዋጋ የሚከፈልባቸውን የሰውና የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትን፣ ማሽኖችን ከቀረጥ ነፃ ማስገባት፣ የብድር አቅርቦት፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት እና የመሠረተ ልማት ግንባታዎችን እንደማበረታቻ በማቅረብ ትልልቅ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ፋብሪካዎቻቸውን ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲከፍቱ ጥረቶች ተደርገዋል፡፡

በእርግጥም ኢትዮጵያ የአፍሪካ የማምረቻ መናኸሪያ (Manufacturing Hub) እንድትሆን የሚደረገውን ጥረት ለማቀላጠፍ እንዲሁም የሥራ አጥነት ችግርን ለመቅረፍ ላቅ ያለ ሚና ይጫወታል ተብሎ የተጣለበት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ውጤት ማስመዝገብ ችሏል፡፡ በተለይም ኢንዱስትሪ ፓርኮቹ ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድሎችን በመፍጠር ቀላል የማይባል አስተዋፅዖ አበርክተዋል። በአሁኑ ወቅት በመላ አገሪቱ 13 የኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚገኙ ሲሆን በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትና በቴክኖሎጂ ሽግግር ለአገራዊ ምጣኔ ሀብት እድገት ቀላል የማይባል አስተዋፅዖ እያበረከቱ ይገኛሉ፡፡

በተለይም የግብርና ውጤቶችን እሴት በመጨመር በብዛትና በጥራት ተወዳዳሪ የማድረግ አቅም እንዳላቸው የታመነባቸው የተቀናጁ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ((Integrated Agro-Industry Parks)፣ የግብርናውን ዘርፍ በማዘመን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግርን ያሳካሉ ከተባሉ የኢንዱስትሪ ፓርክ ዘርፎች መካከል በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ የአግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች ለአርሶ አደሮች የግብይት ሰንሰለቱን ቀላል በማድረግ አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የገበያ ትስስር ይፈጥራሉ፡፡ ባለሀብቶች የግብርና ግብዓቶችን ከአርሶ አደሮች እንዲቀበሉ በማድረግ አርሶ አደሮች የልፋታቸውን ያህል እንዲጠቀሙ አወንታዊ አስተዋፅዖ ያበረክታሉ፡፡ መንግሥት አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ለመገንባት እስካሁን ድረስ ከ30 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ማድረጉንና ይህ ወጪ ባለሀብቶች በፓርኮቹ ውስጥ ገብተው በምርት ሥራዎች ላይ እንዲሰማሩ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር እንደሆነ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በኦሮሚያ ክልል፣ ምሥራቅ ሸዋ ዞን፣ አዳሚ ቱሉ ጂዶ ኮምቦልቻ ወረዳ፣ ከባቱ ከተማ በ16 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘው የ«ቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ» በአገሪቱ ከተገነቡ የተቀናጁ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች መካከል አንዱ ነው። ፓርኩ በሚያዝያ ወር 2013 ዓ.ም በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የተመረቀ ሲሆን፤ የአትክልትና ፍራፍሬ፣ የወተት፣ የማር፣ የስጋና የእንቁላል ምርቶችን የሚያቀነባብሩ አምራቾች የሚሰማሩበት የኢንዱስትሪ ፓርክ ነው፡፡ የፓርኩ የመጀመሪያ ዙር ግንባታ በ271 ሄክታር መሬት ላይ ያረፈ ሲሆን፣ እስከ አንድ ሺ ሄክታር መሬት መሸፈን የሚችሉ ቀጣይ ዙር ግንባታዎች ሊከናወኑለት እንደሚችል የፓርኩ የአዋጭነት ጥናት ያሳያል፤ ፓርኩ በሙሉ አቅሙ ወደ ሥራ ሲገባ ከ70ሺ እስከ 100ሺ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጥራል ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በኦሮሚያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የሕዝብ ግንኙነት ባለሙያ አቶ ጌታሁን አዱኛ እንደሚናገሩት፣ የቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ባለሀብቶችን ተቀብሎ ለማስተናገድ ባከናወናቸው ተግባራት አንዳንድ አምራች ኩባንያዎች ወደ ፓርኩ ገብተው በግብርና ምርቶች ማቀነባበር ሥራ ላይ ለመሰማራት የሚያስችሏቸውን የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እያከናወኑ ይገኛሉ፤ በማር ምርት ማቀነባበር ላይ የተሰማራ አንድ አምራች ድርጅት ደግሞ ምርቶቹን ለአገር ውስጥ ገበያ ማቅረብ ጀምሯል፡፡ ድርጅቱ በቀጣይ ምርቱን በስፋት በማምረት ለውጭ ገበያ የማቅረብ አቅድ አለው፡፡

«24 አምራቾች በፓርኩ ውስጥ ገብተው ለመሥራት በተለያዩ የሥራ ደረጃዎች ላይ ይገኛሉ፡፡ ኢንቨስተሮቹን ተቀብለን የውል ስምምነት ፈፅመናል፡፡ አምራቾቹ ከባንክና ሌሎች ዘርፎች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በመጨረስ ላይ ይገኛሉ፤ ሼድ በመገንባት እና ማሽኖችን በመትከል ላይ የሚገኙ አምራቾችም አሉ፡፡ በቅርብ ጊዜ ውስጥ ጨርሰው ወደ ሥራ ይገባሉ፡፡ ባለሀብቶቹ የሚሰማሩባቸው የአግሮ-ፕሮሰሲንግ (ግብርና ማቀነባበር) ዘርፎች የማርና ሰም፣ የምግብ ዘይት፣ የአትክልትና ፍራፍሬ (ቲማቲም፣ ድንች፣ ጭማቂ...)፣ የቡና፣ የአቮካዶ ዘይት፣ የስጋ፣ የወተት፣ የእንስሳት መኖ፣ የፓስታና ማካሮኒ፣ የሕፃናት ምግቦች ማምረትና ማቀነባበር ሥራዎች ናቸው፡፡ እነዚህ አምራቾች ያስመዘገቡት አጠቃላይ የካፒታል መጠን 19 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር ሲሆን፣ ወደ ሥራ ሲገቡ ከ10ሺ እስከ 20ሺ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጥራሉ ተብሎ ይጠበቃል» ብለዋል፡፡

የኢንቨስትመንት ተግባራት ማኅበረሰቡን በሥራ ዕድል ፈጠራ፣ በምርትና አገልግሎት አቅርቦት፣ በመሠረተ ልማት ዝርጋታ፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር እና በገበያ ዕድል ተጠቃሚ እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡ የተቀናጁ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርኮችም በተገነቡባቸው አካባቢዎች የሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በልዩ ልዩ መንገዶች ተጠቃሚ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

አቶ ጌታሁን እንዳሉት፤ የቡልቡላ የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ የግብርውን ዘርፍ ለማሳደግ ታልሞ የተገነባ በመሆኑ የአገር ውስጥ የግብርና ምርቶችን በግብዓትነት ይጠቀማል፡፡ በፓርኩ አካባቢ ያለው ማኅበረሰብ አርሶ አደር እንደመሆኑ የፓርኩ አምራቾች የሚጠቀሙት ጥሬ ዕቃ የአካባቢውን የግብርና ምርት ነው፡፡ አርሶ አደሩ ግብርናውን በማዘመንና አምራችነቱን በመጨመር ለምግብና ለገበያ ከሚያውለው ምርት በተጨማሪ ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆን ትርፍ ምርት እንዲያመርት እየተሠራ ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት በፓርኩ ውስጥ ሥራ የጀመረው የማር ማቀነባበሪያ ፋብሪካ በመሆኑ በክልሉ ከሚገኙ ብዙ የማር አምራች ኅብረት ሥራ ማኅበራት ጋር የገበያ ትስስር ፈጥሯል፡፡ በቀጣይ ተጨማሪ አምራቾች በስጋ፣ በዶሮ፣ በወተት፣ በጥራጥሬ፣ በዘይትና በሌሎች ዘርፎች ወደ ሥራ ሲገቡ አርሶ አደሩ ይበልጥ ተጠቃሚ ይሆናል ነው ያሉት፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በአገር ውስጥ ምርት በመተካት የአካባቢው ኅብረተሰብ የገበያ ዕድል እንዲያገኝ ያደርጋል በማለት ፓርኩ ለአካባቢው ማኅበረሰብ እያበረከተ ያለውን ፋይዳ አስረድተዋል፡፡

እንደአቶ ጌታሁን ገለፃ፣ ከፓርኩ ጋር ትስስር ያላቸውና ግንባታቸው የተጠናቀቀ ስድስት የገጠር ሽግግር ማዕከላት ያሉ ሲሆን፤ የማዕከላቱ ዋና ተግባር የአርሶ አደሩን ምርት በጥራትና በብዛት ሰብስቦ ለፓርኩ አምራቾች ማቅረብ ነው፡፡ ወደ ፓርኩ የሚገቡት ባለሀብቶች ከሽግግር ማዕከላቱ ጋር በሚፈጥሩት ትስስር አርሶ አደሩን ጨምሮ የአካባቢው ኅብረተሰብ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

በሲዳማ ክልል የሚገኘው የ«ይርጋለም የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ»ም የግብርና ምርቶችን የሚያቀነባብሩ አምራቾች የሚሰማሩበት የኢንዱስትሪ ፓርክ ነው፡፡ የፓርኩ የመጀመሪያ ምዕራፍ ግንባታው በ2013 ዓ.ም በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተመርቆ ሥራ እንደጀመረ ይታወሳል፡፡

በአገሪቱ ከሚገኙ የአግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች መካከል ቀድሞ ወደ ሥራ የገባው ይህ ፓርክ፣ 152 ሼዶችን መያዝ የሚችል የለማ መሬት የተዘጋጀለት ነው። ግንባታው በሦስት ምዕራፎች ተከፋፍሎ የሚከናወነው ፓርኩ በ294 ነጥብ አምስት ሄክታር መሬት ላይ አርፏል። ፓርኩ (በሲዳማ ክልል ሦስት እና በጌዴኦ ዞን ሦስት) በድምሩ ስድስት የገጠር ሽግግር ማዕከላት አሉት፡፡

በሲዳማ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የቢዝነስ ልማትና ኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ጴጥሮስ ማርቆስ እንደሚናገሩት፤ በይርጋለም የተቀናጀ አግሮ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ 500 ሚሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡና ወደ ሥራ የገቡ አራት አምራቾች አሉ፡፡ ሁለቱ በአቮካዶ፣ አንዱ በወተት እንዲሁም አንዱ በማር ምርትና ማቀነባበር ተግባራት ላይ ተሰማርተዋል፡፡ ከእነዚህ ኩባንያዎች በተጨማሪ በቡና፣ በአትክልትና ፍራፍሬ ማቀነባበር እና በሌሎች ዘርፎች ላይ የሚሰማሩ ሌሎች 26 ባለሀብቶች ወደ ፓርኩ ለመግባት የሚያስችላቸውን ስምምነት ፈርመዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል ሁለት በቡና ማቀነባበር ተግባር ላይ የሚሰማሩ ድርጅቶች ማሽኖቻቸውን በመትከል ላይ ይገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ ምርት የጀመሩትና ስምምነት የፈረሙት የፓርኩ አምራቾች ከሦስት ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል አላቸው፡፡ በፓርኩ ውስጥ ገብተው ሥራ የጀመሩ አምራቾች ከሰባት ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ ዕድል ፈጥረዋል፡፡ ወደ ፓርኩ ለመግባት ስምምነት የተፈራረሙ አምራቾች ሥራ ሲጀምሩ ከ58 ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች (ስምንት ሺ ቋሚ እና ከ50 ሺ በላይ ጊዜያዊ) የሥራ ዕድል ይፈጥራሉ፡፡

የይርጋለም የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ ለአካባቢው ኅብረተሰብ ብዙ ጥቅሞችን እያስገኘ እንደሆነ የገለጹት አቶ ጴጥሮስ፤ ከዚህ ቀደም አርሶ አደሮች አቮካዶ ለነጋዴዎች ሲሸጡ በዝቅተኛ ዋጋ ያቀርቡ እንደነበር አስታውሰው፣ ግብዓቱን በቀጥታ ለፓርኩ አምራቾች ሲያቀርቡ ግን የተሻለ ገቢ ማግኘት እንደቻሉ ነው ያስረዱት፡፡ ከገበያ ዕድል በተጨማሪ የአካባቢው ኅብረተሰብ በሥራ ዕድል ተጠቃሚ እየሆነ እንደሚገኝ እና አምራቾቹም ለአካባቢው ኅብረተሰብ የተለያዩ ድጋፎችን እንደሚያደርጉም ተናግረዋል፡፡

የይርጋለም የተቀናጀ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት ረገድ ተጠቃሽ የሆነ አግሮ-ኢንዱትሪ ፓርክ ነው የሚሉት አቶ ጴጥሮስ «በፓርኩ ውስጥ ተመርተው ለውጭ ገበያ ከቀረቡ ምርቶች ስድስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ዶላር ገቢ መገኘቱንም አመላክተዋል፡፡ ኩባንያዎቹ አምርተው ለገበያ ያዘጋጁት ምርት ለገበያ ሲቀርብ ደግሞ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

የአገሪቱን የምጣኔ ሀብት መዋቅር ከእርሻ መር ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለማሸጋገር የሚያግዙ በርካታ መልካም አጋጣሚዎችና ዕድሎች አሉ፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህን መልካም አጋጣሚዎች በመጠቀም የኢኮኖሚውን መዋቅራዊ ሽግግር ለማሳካት የተከናወኑ ተግባራት አገሪቱ ካላት አቅምና ፍላጎት ጋር ተመጣጣኝ አይደሉም፡፡ ኢትዮጵያ በኢንዱስትሪ ያላትን አቅም በመጠቀምና ከዚሁ ዘርፍ የሚገኘውን ገቢ በማሳደግ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የምታደርገውን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግር ለማሳካት አምራች ዘርፉ አሁን ካለው አፈፃፀም በብዙ እጥፍ እንዲጨምርና እንዲሻሻል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የዘርፉ እድገት ሊሻሻል የሚችለው ከኢንቨስትመንት መስፋፋት ጋር ተያይዞ ነው፡፡ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ደግሞ የአንድ ማዕከል አገልግሎትን ተግባራዊ በማድረግ ለኢንቨስትመንት መስፋፋት ምቹ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ ናቸው፡፡ ስለሆነም መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግሩን ለማሳካት የኢንዱስትሪ ፓርኮችን አፈፃፀም ማሻሻል ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ የግብርናውን ዘርፍ በማዘመን ኢንዱስትሪ መር ምጣኔ ሀብትን ለመገንባት ጠንካራ ግብዓት ለሚሆኑት የተቀናጁ አግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ላቅ ያለ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ትኩረትም ባለሀብቶች ወደ ፓርኮቹ ገብተው ለማምረት የሚያስችሏቸውን የመሠረተ ልማት ግብዓቶች፣ የሰለጠነ የሰው ኃይልና የፋይናንስ አቅርቦት ማሟላትን እንደሚያካትት ሊታወቅ ይገባል፡፡

የግብርና ውጤቶችን እሴት በመጨመር በብዛትና በጥራት ተወዳዳሪ የማድረግ አቅም እንዳላቸው የታመነባቸው የተቀናጁ የግብርና ምርቶች ማቀነባበሪያ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ((Integrated Agro-Industry Parks)፣ የግብርናውን ዘርፍ በማዘመን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግርን ያሳካሉ ከተባሉ የኢንዱስትሪ ፓርክ ዘርፎች መካከል በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ። እነዚህ የአግሮ-ኢንዱስትሪ ፓርኮች ለአርሶ አደሮች የግብይት ሰንሰለቱን ቀላል በማድረግ አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ የሚያደርግ የገበያ ትስስር ይፈጥራሉ፡፡ ባለሀብቶች የግብርና ግብዓቶችን ከአርሶ አደሮች እንዲቀበሉ በማድረግ አርሶ አደሮች የልፋታቸውን ያህል እንዲጠቀሙ አወንታዊ አስተዋፅዖ ያበረክታሉ

# ጎሜ

# ወይ ስንዴ !

እስማኤል አረቦ

‹‹ጤፍ፤ ገብስ፤ ማሽላ፤ ሳመርት ማንም ከቁብ ያልቆጠረኝ ምነው ስንዴ ስዘራ ሁሉም ፊቱን አጠቆረብኝ፡፡ ምነው ምቀኛዬ በዛ፤ ወዳጄ የነበረው ሁሉ ምን ነክቶት ነው በአንድ ጊዜ ጠላት የሆነብኝ›› እያለ አርሶ አደር ጣሰው በለሆሳስ ይናገራል፡፡ ታታሪው አርሶ አደር ጣሰው ከንደ ብርቱ ወዳጅ ይመስሉ የነበሩ ሁሉ ስንዴ በማምረቱ በክፉ ዓይናቸው ማየት እንደጀመሩት ቀልቡ ነግሮታል፡፡

ይህ ጉዳይ በአርሶ አደር ጣሰው ላይ ብቻ የተፈጸመ አይደለም፡፡ ከግለሰብም አልፎ አገርም የታመመችበት ጉዳይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ስንዴ ማምረቷና ወደ ጎረቤት አገር መላኳ የከነከናቸው ብዙዎች ናቸው፡፡ ለወትሮ ወዳጅ የሚመስሉት ሁሉ ዛሬ በጠላትነት መገለጥ ጀምረዋል፡፡ ምስጢሩ ደግሞ ይሄ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ለዘመናት ያህል ነፃነቷን ጠብቃ የኖረች የጥቁር ሕዝቦች ተምሳሌት ብትሆንም በምግብ ሰብል እራሷን ባለመቻሏ ነፃነቷን በሚገባ ሳታጣጥም ኖራለች። በዓድዋ የተገኘው ድል በቅኝ ገዢዎች የፈረጠመ ኢኮኖሚ ሲጠመዘዝ ኖሯል፡፡ የኢትዮጵያ ኩራትና ድል በስንዴ ልመና ኮስሶ ቆይቷል፡፡ ዛሬ ግን የዓድዋ ድል በተገቢው ቦታው ላይ እንዲነግስ የሚያስችል አኩሪ ታሪክ መጻፍ ጀምሯል፡፡ ኢትዮጵያ ዳግም ነፃነቷን በስንዴ ማወጅ ቀጥላለች፡፡ ከስንዴ ጠባቂነት ወደ ስንዴ ላኪነት ተሸጋግራለች፡፡

ስንዴ ከሩዝ ቀጥሎ በዓለማችን በስፋት የሚመረት የሰብል ዓይነት ነው፡፡ በዓለም ላይ ከሚታረሰው የመሬት መጠንም 15 በመቶ የሚሸፈነው በስንዴ ነው። ስንዴ በባህላዊ መንገድ ተፈጭቶ ለቂጣ፤ ለገንፎ፤ ለተለያዩ መጠጦች መሥሪያ ከማዋሉም ባሻገር በፋብሪካ ተቀነባብሮ ለፓስታ፤ ለማካሮኒ፤ ለብስኩትና ለተለያዩ መድኃኒቶች መሥሪያ ይውላል፡፡

ስንዴ በዓለማችን ላይ በድሃም ሆነ በሀብታም አገራት እጅግ ተፈላጊ የሆነ ሰብል ነው፡፡ ከምግብነቱ ባሻገርም እንደነዳጅ ሁሉ ከፍተኛ ገንዘብ አምጪ የሆነ ሀብት ነው፡፡ በስንዴ ምርት ውጤታማ የሆነ አገር አስተማማኝ የገንዘብ ምንጭ ከመፍጠሩም ባሻገር ነፃነቱን እንዳረጋገጠ ይቆጠራል፡፡ ከተረጂነት ነፃ የመሆንና እራስን የመቻል ተምሳሌት ነው፡፡ ለዚህም ይመስላል በርካታ አገራት ስንዴን ከምግብም በላይ የሆነ ግምት የሚሠጡት፡፡

ኢትዮጵያ በዓለም ላይ ስንዴ ሸማች ከሆኑ አገራት ውስጥ በግንባር ቀደምትነት የምትታወቅ አገር ነበረች፡፡ በየአመቱም እስከ 107 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ በማስገባት 1 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ወጪ ትገፈግፍ ነበር፡፡ ሆኖም ባለፉት አራት አመታት መንግሥት ለስንዴ ምርት በሰጠው ትኩረትም ኢትዮጵያ ስንዴን ከውጭ ማስገባት ከማቆሟም ባሻገር ወደ ውጭ መላክ ጀምራለች፡፡ ይህ ጥረቷም በዓለም ላይ ስንዴ በማምረት ተጠቃሽ ከሆኑ 18 አገራት ተርታ አሰልፏታል፡፡ ኢትዮጵያ ከስንዴ ተቀባይነት ወደ ስንዴ ላኪነት እራሷን በመለወጥም ታሪክ ሠርታለች፤ለቀጣናው አገራትም ኩራት ሆናለች፡፡

ይህ ደግሞ ኢትዮጵያ ሁልጊዜ ተመጽዋች ሆና እንድትቀጥል ለሚፈልጉ ወገኖች የሚዋጥላቸው አልሆነም፡፡ ኢትዮጵያ እንደ ዓድዋው ድልሁሉ በስንዴ ላይ ድልን ከተቀዳጀች ዳግም ነፃነቷን እንዳወጀች የሚቆጠር ነው፡፡ ይህ የኢትዮጵያ ግስጋሴ ምጽዋትን ለፖለቲካ ጥቅማቸው በማዋል አገራትን ማንበርከክ ለሚፈልጉ አገራት ደግሞ የመርዶ ያህል አስደንጋጭ ነው። በዚህ የደነገጡ አገራት ደግሞ ከአምና ጅምሮ በርካታ ጻያፍ ተግባራትን ሲከውኑ ከርመዋል፡፡

ኢትዮጵያ ስንዴ አምርታ ወደ ኬንያ እንደምትልክ ባስታወቀች ማግስት ኬንያ በዘመኗ አይታ የማታውቀውን የስንዴ እርዳታ እንዲጎርፍላት ተደርጓል፡፡ በግብረሰናይ ስም የገቡ ለጋሽ ነን የሚሉ አገራት ተላላኪዎችም ስፍር ቁጥር የሌለው ገንዘብ እየረጩ አርሶአደሩ ስንዴ ለመንግሥት እንዳይሸጥ በርካታ አፍራሽ ሥራዎችን ሲሠሩ ቆይተዋል፡፡ በአጠቃላይ ከጅምሩ ጀምሮ ‹‹ኢትዮጵያ ስንዴን እንኳን ለውጭ ገበያ ልታቀርብ ቀርቶ እራሷም በርሃብ ውስጥ ነች ያለችው፤ ስንዴ አምርታ ወደ ውጭ መላክ አይሳካላትም›› የሚሉ ሀሰተኛ ዜናዎችን በማሰራጨት መንግሥት የጀመረውን ጥረት ለማኮላሸት ረጅም ርቀት ተጉዘዋል፡፡

መንግሥት የጀመረውን የስንዴ ልማት ለማደናቀፍና አሁንም ኢትዮጵያ እርዳታ ጠባቂ አገር ናት ለማስባልም የማይፈነቀል ድንጋይ የለም፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎንም የእርዳታ ስንዴ ተሰርቋል በሚል ሰበብም በኢትዮጵያ በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ለተፈናቀሉ ወገኖች ይቀርብ የነበረው ዕርዳታ እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡ በዚሁ ሰበብም በርካታ ንጹሃን ዜጎች ማግኘት የሚገባቸውን እርዳታ በወቅቱ እንዳያገኙ ከማድረጉም ባሻገር በቀጣይ ከፍተኛ የሆነ እርሃብ እንዳይከሰት ስጋት ደቅኗል፡፡ በተለይም ደግሞ እርዳታ የተቋረጠባቸው አካባቢዎች ለሁለት አመታት ያህል በዘለቀ የሰሜኑ ጦርነት ውስጥ የነበሩና አሁንም ጦርነቱ ካስከተለባቸው ሥነልቦና ያልተላቀቁ መሆኑ ችግሩን የከፋ ያደርገዋል፡፡

እርዳታና ፖለቲካ በተደበላለቀበት የምዕራቡ ዓለም ዜጎች ሲቸገሩ እየታየ በፖለቲካ መነጽር ብቻ በመመልከት እርዳታን መንፈግ ከሰብዓዊነትም በታች ነው፡፡ በተባበሩት መንግሥታት ድንጋጌ መሠረት ሰው ሰራሽም ሆነ ሰው ሰራሽ ባልሆነ ምክንያት የተፈናቀሉና ለችግር የተጋለጡ ሰዎች ሰብአዊ እርዳታ የማግኘት መብት እንዳላቸው ቢደነገግም ይህንኑ ድንጋጌ በመተላለፍ የፖለቲካ እሳቤም ሆነ ድርጊት ውስጥ ምንም ተሳትፎ የሌላቸው ሰዎች ሲቀጡ መመልከት የተለመደ ሆኗል፡፡

ሆኖም ግመሎቹም ይጓዛሉ፤ውሻዎችም ይጮሃሉ እንደሚለው ተረት ኢትዮጵያ አርሶ አደሩን ከመሬቱ ጋር በማስማማት ማሳውን በሙሉ በስንዴ መሸፈን ችላለች፡፡ አርሶ አደሩም የስንዴን ጠቀሜታ እየተረዳ በመምጣቱም ከሌሎች ሰብሎች በተለየ ለስንዴ ትኩረት ሰጥቶ መሬቱን በማረስ ላይ ይገኛል፡፡

ኢትዮጵያ በምግብ እህል ራሷን መቻል አቅቷት ቢሊዮን ዶላር አውጥታ ከውጭ ከማስገባት በዘለለ፣ ለዕርዳታ የብዙዎችን በር ስታንኳኳም ሰንብታለች። አንዳንድ ጊዜም ረጂ አገራት ስንዴን እንደመያዣ አድርገው የሚፈልጉትን ሁሉ ለመጫን ሲሞክሩ ታይተዋል፡፡ ሆኖም ይህ ታሪክ ያበቃ ይመስላል፡፡

በተያዘው አመት ኢትዮጵያ 129 ሚሊዮን ኩንታል የሚጠጋ የስንዴ ምርት ታመርታለች፡፡ 97 ሚሊዮን ኩንታል የሚሆን ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚውል ሲሆን 32 ሚሊዮን የሚጠጋው ወደ ውጭ ተልኮ ዶላር የሚያስገኝ ነው፡፡ ለዚህም ዘንድሮ ሱዳንና ኬንያን ጨምሮ ስንዴ የመግዛት ፍላጎት ያላቸው ስድስት አገራት ጋር የ3 ሚሊዮን ኩንታል የውል ስምምነት ተፈርሟል። የረድኤትና ሌሎች የአገር ውስጥ ድርጅቶች ከውጭ የሚገዙትን በአገር ውስጥ እንዲተኩ በገንዘብ ሚኒስቴር በኩል የ2 ነጥብ 9 ሚሊዮን ኩንታል የውል ስምምነት በመፈረም ላይ መሆናቸው ተነግሯል፡፡ በዚህም ኢትዮጵያ ከ200ሚሊዮን ዶላር በላይ ገቢ እንደምታገኝ ይገመታል፡፡

ይህ የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ከማሳደግ ባሻገር የጎረቤት አገራት ከአውሮፓ፤ ከአሜሪካና ካናዳ ደጅ ጠንተው የሚገዙትን ስንዴ ከደጃቸው በቀላሉ እንዲያገኙ ያስችላቸዋል፡፡ የምሥራቅ አፍሪካን አካባቢም ከግጭትና ሁከት በማውጣት አገራቱን በልማት እንዲተሳሰሩ በር ይከፍታል፡፡

ኢትዮጵያ እያካሄደች ያለችው የስንዴ ምርት ግስጋሴ ቀጥሏል፡፡ ዓምናና ዘንድሮ 2.8 ሚሊዮን ሔክታር በስንዴ ማሳ የተሸፈነ ሲሆን በበጋ ወቅት ይመረታል ተብሎ የታሰበ 50 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴን ሳይጨምር ከ108 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የስንዴ ምርት ይገኛል ተብሎ ይታሰባል፡፡

በዓለም ላይ እጅግ ውድ እና ተፈላጊ የሆነውን አዝርዕት ኢትዮጵያ ከማምረትም አልፋ ለውጭ ገበያ እነሆ ብላለች፡፡ ስንዴ የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥ ረገድ ቁልፍ የምግብ ዘርፍ ሲሆን የአምራች አርሶ አደሮችን ገቢ በማሳደግ፤ የሥራ ዕድልን በመፍጠርና አገራዊ ገቢን በማሳደግ የማይተካ ሚና አለው፡፡

ስንዴ ለኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ ብቻ ሳይሆን በአገር ውስጥ ያሉ ኢንዱስትሪዎች እንዲነቃቁ የሚያስችል ሞተር ነው፡፡ የኢንዱስትሪ ሚኒስትሩ አቶ መላኩ አለበል እንደተናገሩትም፤ የስንዴ ልማቱ በአገር ውስጥ ላሉ ከ440 በላይ ኢንዱስትሪዎች ግብዓትን ሙሉ በሙሉ በአገር አቅም መሸፈን የሚያስችል ነው።

ኢትዮጵያ
እንደ ዓድዋው ድልሁሉ
በስንዴ ላይ ድልን
ከተቀዳጀች ዳግም
ነፃነቷን እንዳወጀች
የሚቆጠር ነው። ይህ
የኢትዮጵያ ግስጋሴ
ምጽዋትን ለፖለቲካ
ጥቅማቸው በማዋል
አገራትን ማንበርከክ
ለሚፈልጉ አገራት ደግሞ
የመርዶ ያህል አስደንጋጭ
ነው።በዚህ የደነገጡ
አገራት ደግሞ ከአምና
ጀምሮ በርካታ ጸያፍ
ተግባራትን ሲከውኑ
ከርመዋል

ኢትዮጵያ ለስንዴ ምርት የሚሆን ምቹ የአየር ጸባይና ለም አፈር አላት፡፡ ይህንኑ አቅሟን በመጠቀምና ቴክኖሎጂን ከክላስተር የእርሻ አስተራረስ ዘዴ ጋር በማቀናጀት በተሠራው ሥራ ኢትዮጵያን ከስንዴ ተቀባይነት ወደ ስንዴ ላኪነት አሸጋግሯታል፡፡ ስንዴ በሁሉም የአገሪቱ ክፍል የሚመረት ቢሆንም በዋናነት ግን በኦሮሚያና በአማራ በስፋት ይመረታል፡፡ በአገሪቱ ከሚመረተው የስንዴ ምርት ውስጥ 54 ነጥብ 4 በመቶ ከኦሮሚያ የሚገኝ ሲሆን 27 በመቶ ከአማራ፤ 8ነጥብ 7 በመቶ ከደቡብ ሕዝቦች እንዲሁም 6ነጥብ 2 በመቶ ከትግራይ የሚገኝ ነው፡፡

በቀጣይም መንግሥት ለዘርፉ በሰጠው ትኩረትም የሶማሌ፤ የቤኒሻንጉል፤ አፋር፤ ጋምቤላ፤ ሲዳማን የመሳሰሉት ክልሎች ኃይላቸውን አስተባብረው ስንዴን ማምረት ጀምረዋል፡፡ የእነዚህ አካባቢዎች ምርታማነት ሲጨምርም ኢትዮጵያ በአፍሪካም ሆነ በዓለም ላይ ያላት ስንዴን የማምረት ታሪክ በእጅጉ የሚቀይረው ይሆናል፡፡

አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ እንኳን ኢትዮጵያ በአፍሪካ ከደቡብ አፍሪካ ቀጥላ ሁለተኛዋ ስንዴ አምራች አገር ለመሆን አብቅቷታል፡፡ የአፍሪካ አገራት ስንዴን ከውጭ በመቀበል የሚታወቁ ናቸው፡፡ ስንዴንም ለማግኘት በርካታ ውጣውረዶችን ማለፍ ይገባቸዋል፡፡ በዩክሬንና በራሽያ ጦርነትም በግልጽ እንደታየው በዓለም ላይ በሚነሱ መስተጓጎሎች የቅድሚያ ተጠቂዎቹ የአፍሪካ አገራት ሆነው ተገኝተዋል፡፡ በዩክሬንና በራሽያ ጦርነትም በተከሰተው የስንዴ እጥረት እስከ 300 ሚሊዮን የአፍሪካ ሕዝብ ለርሃብ እንደሚጋለጥ ዓለም አቀፍ ተቋማትና ግዙፍ ሚዲያዎቻቸው ጭምር በስፋት የዘገቡት ነው፡፡

ስለሆነም ኢትዮጵያ ስንዴ አምራችና ላኪ አገር መሆኗ በስጋት ውስጥ ላሉት የአፍሪካ አገራት ትልቅ እፎይታን ይዞ የሚመጣ ነው፡፡ ይህንኑ ሃቅ መሠረት በማድረግም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) በአፍሪካ ኢትዮጵያን ጨምሮ ከ250 ሚሊዮን በላይ እርዳታ ፈላጊዎች መኖራቸውን በመጥቀስ «ኢትዮጵያን ኤይድ» በሚል ስንዴ ለመለገስ ተግተን እንሠራለን ነው ያሉት። በዓለም ላይ የተፈጠረውን የስንዴ ገበያ ችግር ለማቃለልም ኢትዮጵያ የበኩሏን እንደምትወጣ ገልጸዋል።

Index box market intelligence የተሰኘ የመረጃ መረብ ይፋ እንዳደረገውም የአፍሪካ አገራት የስንዴ ፍላጎት እየጨመረ ነው፡፡ እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2012 ብቻ የአፍሪካውያን የስንዴ ፍላጎት በ1 ነጥብ 3 በመቶ ጨምሯል፡፡ ይህ አሃዝ በቀጣዮቹ አመታት እንደሚጨምር የመረጃ መረቡ ትንበያውን አስቀምጧል፡ ፡ ይህ ደግሞ እንደኢትዮጵያ ላሉ ስንዴ አምራችና ላኪ አገራት ጥሩ ዕድል ይዞ የሚመጣ ነው፡፡

ወደ አፍሪካ ከሚገባው ስንዴ ውስጥ 50 በመቶ የሚሆነውን ምርት የሚወስዱት ናይጄሪያ፤ አልጄሪያና ግብጽ ሲሆኑ የጎረቤታችን ኬንያ ፍላጎትም በየጊዜው እየጨመረ መጥቷል፡፡ ዘንድሮም ኢትዮጵያ ኬንያን ጨምሮ ወደ ስድስት አገራት የስንዴ ምርቷን ለመላክ ዝግጅቷን ጨርሳለች፡፡

ላለፉት ሁለት አመታት ኢትዮጵያ በጦርነት ውስጥ ብትቆይም ከጦርነቱ ጎን ለጎን ስንዴን፤ አረንጓዴ ዐሻራ፤ የተለያዩ የቱሪስት መስህቦችንና የህዳሴ ግድብን የመሳሰሉ ግዙፍ የኃይል ፕሮጀክቶችን በመገንባት አይበገሬነቷን አሳይታለች፡፡ እንደበርካቶች እምነትም ጦርነቱ በሚፈጥረው ቁርሾ አገር ትበታተናለች፤ ኢትዮጵያ የሚባለው ስምም ከመቃብር በታች ይወርዳል ብለው ቢያልሙም በተቃራኒው ኢትዮጵያውያን ችግራቸውን በራሳቸው ባህልና ወግ ፈትተው ለአፍሪካ ምሳሌ ለመሆን በቅተዋል፡፡ በጦርነት ውስጥ የነበሩትም የትግራይ፤ የአማራ እና አፋር አካባቢዎች ሰላም ሰፍኖባቸዋል፡፡ ፊታቸውንም ወደ ልማት አዙረዋል፡፡

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

# ዘመን አይሽሬው የሥነ-ጽሁፍ ፈርጥ በቲያትር

አስናቀ ፀጋዬ

በተባ ብዕሩ ዘመን አይሽሬ የስነ ጽሁፍ ሥራዎችን ለተደራሲን አቅርቧል፡፡ በቀደምት መጽሔቶችና ጋዜጦች ልዩ ልዩ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ወቅታዊ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ጽሁፎችን ለአንባቢያን ጀባ ብሏል፡፡ በውጭ አገራት ተምረው ከመጡ ሌሎች ኢትዮጵያውያን ጋር በመሆን ከንጉስ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ዘንድ ቀርቦ የሥራ መመሪያ ከተቀበለ በኋላ ‹‹የዛሬይቱ ኢትዮጵያ›› ጋዜጣ አዘጋጅ ሆኖ ሥራውን ጀምሯል፡፡ በዚህም ጋዜጣዋን በይዘቷም ሆነ በቅርጿ ከቀደሙት ዕትሞቿ የተለየችና የተሻለች እንድትሆን አድርጓል፡፡ ወደ ምዕራቡ ዓለም ተሻግሮ የቀሰመው እውቀትም የጋዜጣዋን ተነባቢነት ለማሳደግ አግዞታል፡፡

ከዛም በኋላ በንጉሰ ነገሥቱ ባለቤት በእቴጌ መነን አስፋው ስም የተሰየመችውና በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች ትዘጋጅ የነበረችው የ‹‹መነን›› መጽሔት አዘጋጅ ሆኖ ሰርቷል፡፡ አዳዲስ ጋዜጦችና መጽሔቶች እንዲቋቋሙም ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡ ‹‹Addis Reporter›› የተባለ መጽሔት ዋና አዘጋጅ ሆኖም ሰርቷል። በመቀጠል ደግሞ ወደ አሁኑ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ተዛውሮ የሥነ-ጽሑፍ ክፍል ዋና አዘጋጅ እና የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሆኖ ሰርቷል። የእርሱ ዘመን አይሽሬ ጽሁፎች በጋዜጣው ላይ ተከትበው ዛሬም በጉልህ ደምቀው ይታያሉ፡፡

የዘውዳዊ ሥርዓት አክትሞ የደርግ መንግስት ወደ ስልጣን ከመጣ በኋላ ብዙም ሳይቆይ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጁ ረዳት ሆኖ ተመድቧል፡፡ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ደግሞ የድርጅቱ ዋና ስራ አስኪያጅ ሆኖ አገልግሏል፡፡ የማስታወቂያ ሚኒስቴር ቋሚ ተጠሪ ሆኖ ተሾሞም ሰርቷል፡፡ ይህ ታላቅ የሥነ- ጽሁፍ ሰው ከመፅሄትና ከጋዜጣ ሥራዎቹ ባሻገር በዘመን አይሽሬ የድርሰት ሥራዎቹ ይበልጥ ይታወቃል፡፡

ከድርሰት ሥራዎቹ ውስጥ ደግሞ ከአድማስ ባሻገር፣ ኦሮማይ፣ የቀይ ኮኮብ ጥሪ፣ የህሊና ደውል፣ ደራሲው፣ ሀዲስና የመሳሰሉት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በእነዚህ የሥነ-ጽሁፍ ሥራዎቹ በጊዜው የነበረውን ማህበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታ በራሱ ገፀ ባህሪ ቀርጾ ለአንባቢያን አቅርቧል፡፡ በገላጭ የድርስት አፃፃፍ ስልቱም የበርካታ አንባቢያንን ቀልብ መሳብ ችሏል፡፡ ለአገራችን ዘመናዊ የልብ ወለድ አፃፃፍ ስልት መሰረት ከጣሉ ደራሲያን ውስጥም አንዱ ነው፡፡

በእውነተኛ የሥነ-ጽሁፍ አፃፃፍ ዘዴውም ይታወቃል። በድርሰቶቹ ውስጥ በገለፃቸው የጊዜው ጉዳዮች ማለትም የባላባት አገዛዝ፣ የተማሪዎች እንቅስቃሴና የሕዝብ መስዋትነት ፍንትው አድርጎ የሚገልጽባቸው የመጀመሪያ የድርሰት ሥራዎቹ በተለይም ‹‹የቀይ ኮከብ ጥሪ›› እና ሃዲስ የተሰኙት ሥራዎቹ ዋጋ አስከፍለውታል፡፡ ለገፀ ባህሪያት የሚሰጠው ስብእናም ፍፁም ከመምሰሉም በላይ ህያው ሆነው ያሳያቸዋል፡፡

አሁን ደግሞ በዚህ ዘመን አይሽሬ የሥነ ጽሁፍ ፈርጥ ሕይወት ዙሪያ የሚያውጠነጥንና እርሱን የሚዘክር ‹‹በዓሉ ግርማ ቤርሙዳ›› የተሰኘ ቲያትር በውድነህ ክፍሌ ደራሲነት፣ በዶክተር ተሻለ አሰፋ አዘጋጅነትና በአንዱአለም ደጀኔ (አባቡ) መሪ ተዋናይነት በቅርቡ በሀገር ፍቅር ቲያትር ለተመልካች ሊቀርብ ነው፡፡ በአወዛጋቢ ክስተት በደርግ ዘመን ሕይወቱ እንደተቀጠፈ የሚነገረው ደራሲና ፀሐፊ በዓሉ ግርማ፡፡

የቲያትሩ ደራሲ ፀሐፊ ተውኔት ውድነህ ክፍሌ ለአዲስ ዘመን እንደተናገረው፣ በዓሉ ግርማ በዘመኑ በጋዜጠኝነትም ሆነ በደራሲነት እውነትን በመናገር ረገድ ትልቅ ዋጋ የከፈለ የሥነ-ጽሁፍ ሰው ነው፡፡ ‹‹ነገር ግን እኔን ጨምሮ በዚህ ዘመን ላይ ያለነው የቲያትር ባለሙያዎችና ጋዜጠኞች በዓሉ ግርማ በከፈለው ዋጋ ልክ ስሙን ማንሳት አልቻልንም›› ይላል የቲያትሩ ደራሲ፡፡ በዓሉ በዛ ጊዜ ‹‹የፍፃሜው መጀመሪያ›› የተሰኘ አጭር ልብ ወለድ ጽፎ ነበር፡፡ ይህች ልብ ወለድ በኋላ ላይ በአጭር ልብ ወለድ ስብስብ ላይ ታትማለች፡፡ በዚች አጭር ልብ ወለድ ውስጥ በበዓሉ ግርማ ውስጥ ያሉ ሁለት ማንነቶች ተንጸባርቀዋል፡፡ ለነዚህ ሁለት ማንነቶች በዓሉ ሁለት ስም ሰጥቷቸዋል፡፡

አንደኛው ‹‹ህሊና ይፍረደኝ›› የሚል ገፀ ባህሪው ውስጣዊ ሙግቱ ሲሆን ሁለተኛው ገፀ ባህሪው ደግሞ ‹‹ስንት አየሁ ካለሕይወት›› የሚል ነው፡፡ ልብ ወለዷ በሁለቱ መሀል በአንድ ሰው ውስጥ ያሉ ማንነቶች ሲሟገቱ ታሳያለች፡፡ አንድ ስራን ለመስራት እውነትን ልግለፅ አልግለፅ የሚል ስሜት ያላትም ናት። ያመንኩበትን ላውጣ አላውጣ አይነት ሙግትም ነው በልብ ወለዷ የሚገለጸው፡፡

ይህች አጭር ልብ ወለድ በዓሉ ግርማ ኦሮማይ የተሰኘው የድርሰት ሥራው ከመውጣቱ ሶስት ወር በፊት የተፃፈች ናት፡፡ በዓሉ ኦሮማይን ለንባብ ሲያበቃው ችግር እንደሚገጥመው ያውቅ ነበር፡፡ ለዚህም ማረጋገጫው በዚች አጭር ልብ ወለድ ውስጥ ወደ እውነት መጠጋት አለብኝ፤ ያመንኩትን ፅፌ ማውጣት አለብኝ ብሎ መግለፁ ነው፡፡ በኋም በዚህ ትልቅ ዋጋ ከፍሏል፡፡

በዓሉ ግርማ ከሰራባቸው ከመነን መጽሔት አንስቶ እስከ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ድረስ ያለው እያንዳንዱ ታሪኩ ሲታይ ለነገሮች ተጋፋጭነቱን ያሳያል፡፡ በመነን መጽሔት ሲጽፍ በነበረበት ወቅት የነበረውን መንግስት በመንካቱና እንዳይወጡ የታገዱ ጽሁፎችን በማውጣቱ በተደጋጋሚ ተከሷል፡፡ አብሮ እየኖረ እውነትን መጋፈጥ የሚችል ሰው ነው፡፡ ነገር ግን የበዓሉ ግርማን እውነት በዚህ ዘመን ያሉ የቲያትር ባለሙያዎችና ጋዜጠኞች እስካሁን ሊረዱለት አልቻሉም፡፡


ወድነህ እንደሚናገረው፣ በዓሉ ግርማ የሞቀ ትዳር እያለው በጊዜው ትልቅ ዋጋ የከፈለ ደራሲ ነው፡፡ ይህ የበዓሉ ግርማ ትርጓሜ ደግሞ የትኛውም ዘመን ላይ ሊመጣ ይችላል፡፡ የሥነ ጽሁፍ ስራዎቹ ቢነበቡም የከፈለውን ዋጋ ያህል አልተዘከረም፡፡ እስካሁንም ዝም ተብሎ ቆይቷል፡፡ እንዲያውም ተረስቷል፡፡ ይህን ቲያትር ለመስራት መነሳሳቱ የመጣውም የእርሱን ውለታ ለመክፈል ነው፡፡

የበዓሉ ግርማ ባለቤት ወይዘሮ አልማዝ ሕይወቱ እስካለፈበት ድረስ ሁልጊዜ ማታ ማታ የሚመጣ ይመስላቸው ነበር፡፡ በር በተንኳኳ ቁጥር እድሜ ዘመናቸውን ሙሉ ሲጨነቁ ኖረው ያለፉ ናቸው፡፡ ይህ ቲያትር ቀድሞ ወጥቶ ቢሆን ኖሮ የክብር እንግዳ እርሳቸው በሆኑ ነበር፡፡ ቲያትሩ ለእርሳቸው ትልቅ ትርጉም ይኖረው ነበር፡፡ አሁንም ግን ቲያትሩ ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ትልቅ ትርጉም ያለውና በዓሉ ለከፈለው ዋጋ ቢያንስ የህሊና ምላሽ መስጠት የሚያስችል ብሎም ባለእዳ ከመሆን የሚያድን ነው፡፡ ለከፈለው ዋጋ ትልቅ የቲያትር መነሻ ሆኖም ያገለግላል፡፡

የውድነህ ክፍሌ ‹‹በዓሉ ግርማ ቤርሙዳ›› ቲያትር ድርሰት ከተጀመረ ረጅም ጊዜ ሆኖታል፡፡ እንደውም ሥራው የተጀመረው እርሱ አማተር የቲያትር ባለሙያ እያለ ነበር፡፡ በጊዜው ‹‹በዓሉ ግርማ›› የተባለና አርባ አንድ አባላት ያሉት የኪነ ጥበብ ክበብ በ1980ዎቹ መጀመሪያ ላይ የነበረ ሲሆን የክበቡ የበላይ ጠባቂ የበዓሉ ግርማ ባለቤት ወይዘሮ አልማዝ ነበሩ፡፡ የክበቡ መሪ ደግሞ ራሱ ውድነህ ክፍሌ ነበር፡፡ የበዓሉ ግርማ ልጆች መስከረምና ዘላለምም የክበቡ አባላት ነበሩ፡፡ ከዛ ጊዜ ጀምሮ ታዲያ ውድነህ ክፍሌ ከበዓሉ ግርማ ጋር በተያያዘ በውስጡ በርካታ ነገሮች ነበሩ፡፡ በዩኒቨርሲቲ ቆይታውም የእርሱን አጭርና ረጅም ልብ ወለል ሥራዎች የኮርስ ማሟያ ወረቀቶችን ሰርቶባቸዋል፡፡

ሆኖም ይህን ቲያትር የጀመረው በ2013 ዓ.ም ነው። እስከዛሬ ከፃፋቸው የቲያትር ተውኔቶችም ይህ በብዙ ፈትኖታል፡፡ ምክንያቱም ቲያትሩን ለመስራት ስለ በዓሉ የተፃፉ ታሪኮችን ማንበብና ጥናቶችን ማድረግ ነበረበት። በተለይ ከበዓሉ ግርማ ጋር በተያያዘ በርካታ አወዛጋቢ ነገሮች በመኖራቸው በዛ አወዛጋቢ ክስተት መሃል የተነሳውን እውነት ይዞ እስከ መጨረሻው ድረስ ይዞ በየት ቀዳዳ በኩል ሾልኮ መውጣት እንደሚችል እንደ አንድ ፀሐፊ ተውኔት ትልቅ ጥያቄ በውስጡ ነበር፡፡

የትያትር ድርሰቱ ጥንቃቄና ንባብ ስለሚጠይቅ ውድነህ ክፍሌ ድርስቱ እየተፃፈ በድንገት ለተወሰኑ ቀናት በራሱ ችግር ሳይፅፍ ከወጣ ተመልሶ ለመፃፍ ይቸገር ነበር፡፡ ተመልሶ ወደዛ ስሜት ለመግባትም በበዓሉ ግርማ ዙሪያ የተፃፉ የተለያዩ መጽሐፎችን በድጋሚ ለማንበብ ተገዷል፡፡ ረጅም ጊዜ ከፈጁበት ተውኔቶች ውስጥም ይህ ‹‹በዓሉ ግርማ ቤርሙዳ›› የተሰኘው ቲያትር ነው፡፡ ጥናቱን ሳይጨምር የቲያትር




ድርሰቱን ለመፃፍ ብቻ ስድስት ወር ፈጅቶበታል፡፡ ከአስራ አንድ በላይ ለሚሆኑ ደራሲያንና ጋዜጠኞችም ድርሰቱን አስነብቧል፡፡

ውድነህ ክፍሌ እንደሚገልጸው፣ በቲያትር ዝግጅት ስራ ዶክተር ተሻለ አሰፋ የተሳተፈ ሲሆን የቲያትር ሥራው በሀገር ፍቅር ቲያትር ታሪክ ከፍተኛ ወጪ የጠየቀና ከተለመደው የቲያትር አፃፃፍ ወጣ ያለ ነው። በዚህም ተዋንያንም ጭምር ትልቅ ዋጋ ከፍለዋል። ተዋንያን ለማግኘት በሚደረገው ፍለጋ በተለይም ‹‹ፊያሜታ ጊላይ›› የተሰኘችውን ገፀ ባህሪ ለማግኘት ትልቅ ውጣ ውረድ ነበር፡፡ ማስታወቂያ ወጥቶ ሃያ አምስት ሰዎች ተመርጠው ውድድር ተደርጎ በመጨረሻ ገፃ ባህሪያዋን ማግኘት ተችሏል፡፡

በዚህ ቲያትር በመሪ ተዋናይነት አንዷለም ደጀኔ /አባቡ/ የሚሳተፍ ሲሆን ዝናቡ ገብረስላሴ፣ሰለሞን ሃጎስና ሌሎችም አስራ አምስት የሚሆኑ ወጣትና አንጋፋ የሀገር ፍቅር ቲያትር ተዋንያን ይሳተፉበታል። በቲያትሩ ከሚሳተፉ ተዋንያን በተጨማሪ በበዓሉ ግርማ መጻሕፍት ውስጥ ያሉ እንደ ፊያሜታ፣ ፀጋዬ ኃይለማሪያም፣ ስእላይ፣ ኮሎኔል ታሪኩና ሌሎችም ገፀ ባህሪያትም ብቅ ብለው እንዲታዩ ይደረጋል፡፡ ስለዚህ ቲያትሩ የእውናዊና ምናባዊ ገፀ ባህሪያት ድምር ውጤት ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ አዘጋጁ ይህን ሊገልፅ የሚችል ዳንስ ይዞ መጥቷ፡፡

የቲያትር ድርሰት ሲታሰብ ተገቢነቱ፣ ማራኪነቱና ግልፅነቱ ወሳኝነት አለው፡፡ ከዚህ አኳያ በዚህ የድርሰት ስራ ከቲያትር አምስቱ አላባውያን ውስጥ ሁለቱ በርዕስነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተደርገዋል፡፡ አንዱ አላባ ገፀ ባህሪ ሲሆን በበዓሉ ግርማ ተሰይሟል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ መቼት ሲሆን ‹‹ቤርሙዳ›› በተሰኘው በዓሉ ግርማ ነበረበት ተብሎ በሚገመት የማሰቃያ ቦታ ተገልጿል፡፡ በዚህ መሰረት የሁለቱ ጥምረት የቲያትሩ አርስት ሆኗል፡፡

ሰዎች በበዓሉ ግርማ ጉዳይ ልክ እንደ ቤርሙዳ አዙሪት ውስጥ ነው ያሉት፡፡ በዓሉ ግርማ እንደሞተ ቢያወቁም እንዴት ሊገደል እንደቻለና የት እንደተቀበረ ግን አያውቁም፡፡ አቡነ ቴፍሎስን ያክል ትልቅ አባት ተገድለው አስክሬናቸው ከብዙ ዘመናት በኋላ ተገኝቷል። የታላቁ ደራሲ በዓሉ ግርማ አስክሬን ግን ደብዛው ጠፍቷል፡፡ እስካሁንም አልተገኘም፡፡ ስለዚህ በዚህ ቲያትር ማሳየት የተፈለገው በዋናነት የበዓሉ ግርማን ስብእና ከፍ ማድረግ ሳለ ሆኖ ከተለያዩ ጥናቶች በመነሳት የበዓሉ አሟሟት ሁኔታ ወዴት አቅጣጫ እንደሚያመራ ለመጠቆም ነው፡፡

በዓሉ ግርማ በዛ ጊዜ የፈፀመው ተግባር ዛሬ ለደራሲዎችና ጋዜጠኞች ትልቅ ትምህርት ነው፡፡ እንደ ደራሲና ጋዜጠኛ ምንም የሚያስፈራ ነገር እንደሌለና ላመኑበት ነገር ፊት ለፊት መጋፈጥ እንደሚገባቸው፤ የትኛውንም ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ መሆን እንዳለባቸው የእርሱ ታሪክ አስረጂ ነው፡፡ የዛሬ ጋዜጠኞችና ደራሲያንም ይህን እየሰበሩ ለበዓሉ ግርማ ደግሞ ሐውልት እያቆሙ ነው፡፡

በዚሁ የበዓሉ ግርማ ቲያትር አጋጣሚ ትልልቅ ነገሮችም ወደመዘከር ይመጣሉ፡፡ ለዚህና ለመጪው ዘመን ምንጊዜም ለሙያው ታማኝ ሆኖ መከፈል ያለበት ዋጋ መክፈል እንዳለበትም ቲያትሩ ያስተምራል፡፡ ይህም ይበልጥ ሌሎችንም ያፀናል፡፡

‹‹በዓሉ ግርማ ቤርሙዳ›› የተሰኘውና በዓሉ ግርማ በጊዜው ለሙያው የከፈለውን መስዋትነት ለመዘከርና ከአንዳንድ ጥናቶች በመነሳት በጊዜው እንዴት ሕይወቱ ሊቀጠፍና አስከሬኑ ሊጠፋ እንደቻለ መላምት ለማስቀመጥ የተሰራው ይህ ቲያትር በርካታ የጥበብ አፍቃሪያን በተገኙበት የፊታችን እሁድ ሰኔ 18 ቀን 2015 ዓ.ም በሀገር ፍቅር ቲያትር ለተመልካች ክፍት ይሆናል፡፡

ዜና

# ጠለፋ - በሕግ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከተማ በአንድ ወር ውስጥ የተጠለፉት ሁለት እንስቶች ናቸው፡፡ የሴት ልጅ ጠለፋ በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ ምን ዓይነት ቅጣት ያስከትላል፣ በተቀመጠው ህግ ላይ ክፍተቶች ስለመኖራቸው እና አተገባበሩስ ምን ይመስላል በሚለው ሃሳብ ዙሪያ የህግ ባለሙያዎች ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

ጠበቃና የህግ አማካሪ የሆነት ወይዘሮ ትሩፋት በላይነህ፤ የጠለፋ ወንጀል ለሴት ልጅ የመብት ጥሰት መሆኑን በማንሳት፤ ሴት ልጅ በጠለፋ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቷን ታጣለች ይላሉ፡፡ የመኖር፣ የእኩልነት እና በነጻነት የመንቀሳቀስ መብቷን እንደሚያሳጣት በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ ላይ በግልጽ መቀመጡን ያስረዳሉ፡፡

የጠለፋ ወንጀል አገባታለሁ በሚል ሰበብ እና ለተንኮል ለመጠቀም እንደሚፈጸም የሚገልጹት የህግ ባለሙያዋ፤ በኢፌዴሪ የወንጀል ሕግ አንቀጽ 587 ቀጥር 1 መሰረት ማንም ሰው እድሜዋ ከ18 ዓመት በላይ የሆነች አንዲት ሴትን አገባታለሁ በሚል ሃሳብ በኃይል፣ በማስፈራራት፣ በዛቻ፣ በተንኮል ወይም በማታለል ከጠለፈ ከሶስት እስከ አስር ዓመት ሊደርስ በሚችል ጽኑ እስራት እንደሚቀጣ መደንገጉን ያስገነዝባሉ፡፡

በዚሁ አንቀጽ ቁጥር ሁለት ላይ የተጠለፈችውን ሴት አስገድዶ ከደፈራት ተጨማሪ ቅጣትን እንደሚያስቀጣ መገለጹንም ያነሳሉ፡፡ በተጨማሪም ጠለፋውን ከፈጸመ በኋላ በማስፈራራት፣ በዛቻ፣ በተንኮል ወይም በማታለል ፈቃደኛ እንድትሆን ካደረገ በኋላ በጠላፊውና በተጠላፊዋ መካከል ጋብቻ መፈጸሙ የወንጀል ተጠያቂነትን እንደማያስቀረውም ይገልጻሉ፡፡

ተበዳይዋ በጠለፋው ድርጊት ለደረሰባት ጉዳት አግባብ ባላቸው የፍትሐ ብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሰረት ካሳ የመጠየቅ መብቷ የተጠበቀ መሆኑ በወንጀል ሕጉ አንቀጽ 587 ቁጥር አራት ላይ መስፈሩን ያስረዳሉ፡፡

አንቀጽ 590 ላይ የጠለፋ ድርጊቱን የፈጸመው ለተንኮል ለመጠቀም፣ ለአምንዝራነት፣ ጉልበቷን ለመበዝበዝ፣ ክብረንጽህናዋን ለመጠቀም እና አስገድዶ ለመድፈር ጭካኔ በተሞላበት ከሆነ በዚህ ህግ ላይ ስለ አስገድዶ መድፈር በተደነገገው መሰረት ከባድ ቅጣት የሚያስቀጣ መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡

በአጠቃላይ እድሜዋ ከ18 ዓመት በላይ የሆነች ሴት ከተጠለፈች ከሶስት እስከ 10 ዓመት፣ ዕድሜዋ ከ18 ዓመት በታች ለሆነችና ለአእምሮ ህመምተኛ ሴት ከአምስት እስከ 15 ዓመት ድረስ ጽኑ እስራት እንደሚያስቀጣ በኢፌዴሪ የወንጀል ህግ በግልጽ መቀመጡን ያስረዳሉ፡፡

የተቀመጠው የጠለፋ ወንጀል ህግ በቂ አይደለም የሚሉት ወይዘሮ ትሩፋት፤ ከ25 ዓመት ጀምሮ እስከ እድሜ ልክ ጽኑ እስራት ቢሆን አስተማሪ እንደሚሆን አመላክተዋል፡፡ በፍትሐ ብሔር ሕግ ድንጋጌዎች የተቀመጡት የካሳ ክፍያዎችም በቂ አይደለም ባይ ናቸው፡፡

የቅጣት ጣሪያው ማነስ ብቻ ሳይሆን የአተገባበር ክፍተት እንዳለም የሚገልጹት ባለሙያዋ፤ የቅጣት ማቅለያ በሚል ሰበብ በተቀመጠው ህግ መሰረት ወንጀል ፈጻሚዎች እየተቀጡ እንዳልሆነ ያስረዳሉ፡፡ የጠለፋ ወንጀል የሚፈጸምባቸው ሴቶች ለአካላዊና ስነልቦናዊ ችግሮች ተጋላጭ ይሆናሉ፡፡ ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሁሉም ባለድርሻ አካላት በትኩረት ሊሰራ እንደሚገባ ያሳስባሉ፡፡

የጠለፋ ወንጀልን በዘላቂነት ለመከላከል የህግ ክፍተቶችን፣ አፈጻጸሙን እና አተገባበሩን ማረም፣ ስለሴቶች የሚሰሩ ተቋማትን ማጠናከር፣ ተቋማት ውስጥ የሴቶችን ውክልና ማሳደግ፣ የእምነት ተቋማትና ሚዲያዎች በትኩረት እንዲሠሩ ማድረግ እንደሚገባ ያስረዳሉ፡፡

"ማንም ሰው የኃይል ድርጊት በመጠቀም፣ በብርቱ ዛቻ፣ ህሊናዋን እንድትስት በማናቸውም ሌላ መንገድ መከላከል እንዳትችል በማድረግ ከጋብቻ ውጪ አስገድዶ ከአንዲት ሴት ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት የፈፀመ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል" ሲል መደንገጉን የሚያስረዱት ደግሞ የህግ ባለሙያ አቶ ካፒታል ክብሬ ናቸው፡፡

የጠለፋ ወንጀልን በዘላቂነት መከላከል ከማንም በፊት የሚጠቅመው ማህበረሰቡን ነው የሚሉት አቶ ካፒታል፤ ማህበረሰቡ የጠለፋ ወንጀል የፈጸመን አካል ለህግ እንዲቀርብ ማድረግ፣ ወንጀል የተፈጸመባቸው ሴቶች ድርጊቱን ለህግ እንዲያቀርቡ ግንዛቤ መፍጠርና ሌሎች ሥራዎችንም መስራት ተገቢ ነው ይላሉ፡፡

መንግሥት የጠለፋ ወንጀል እንዳይፈጸም ቀድሞ መከላከል፣ ጠለፋውን የፈጸሙትን አስተማሪ ቅጣት መቅጣት፣ ግብረሰናይ ድርጅቶች ደግሞ በሴቶች ላይ የሚፈጸም ጥቃት እንዲቆም ግንዛቤ መፍጠር እንዳለባቸው ያስረዳሉ፡፡

በሴቶች ላይ የሚደርስን ጥቃት ለመከላከል መንግሥት፣ ግብረሰናይ ድርጅቶች፣ ማህበረሰቡና የእምነት ተቋማት በቅንጅት መስራት እንዳለባቸውም ያሳስባሉ፡፡

# ብሔራዊ ባንክ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሥራውንም እያጠናቀቅን ነው:: ከሊጋሾች አንዳንድ ግብዓቶችን እየጠየቅን ነው:: በወራት ዕድሜ ለህዝብ እንደራሴዎች ይቀርባል:: ስለዚህ ስራው እየተፋጠነ ነው" ብለዋል አቶ ሠለሞን::

በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ከሦስት እስከ አምስት ለሚደርሱ የውጭ ባንኮች ፈቃድ ለመስጠት እቅድ ተይዞ እየተሰራ መሆኑንም አቶ ሠለሞን ገልጸዋል::

እንደ ምክትል ገዥው ገለጻ፤ የውጭ ባንኮች የአገር ውስጥ ባንኮችን ከገበያ እንዳያስወጧቸው የአገር ውስጥ የፋይናንስ ተቋማት አቅም ግንባታ ላይ ሊሰሩ ይገባል፤ለዚህም የተቀመጠ አሰራር መኖሩን አመልክተዋል::

ተቋማቱ ከመደበኛ በጀታቸው ሁለት ከመቶ የሚሆነውን ለአቅም ግንባታ እንዲያውሉትና ይህም ለባንኮች ከረጅም ዓመታት በፊት የተላለፈ መሆኑን፣ አሁንም ድረስ በዚሁ አግባብ ክትትል እንደሚደረግ አቶ ሠለሞን አስረድተዋል::

አሁን ቀድሞ እንደተለመደው መሄድ አይቻልም ያሉት አቶ ሠለሞን፣ ሪፎርም ከተደረገ ወዲህ ብዙ አዳዲስ ነገሮች አሉ፤ በጀት ተመድቦም በሰፊው መስራት አስፈላጊ ነው ብለዋል::

"በተለይም ማን ከማን ጋር መሥራት አለበት፤ ማን ከማን ጋር ቢዋሃድ ያዋጣል የሚለውን ከአሁኑ ማሰብ ይገባል:: ከውጭ ከሚመጡ ተቋማትም ጋር እንዴት በቅንጅት መስራት እንዳለባቸው ከወዲሁ ማሰብ ይጠበቅባቸዋል፤ ካፒታል፣ እውቀት እና ቴክኖሎጂ እንዴት መጋራት እንደሚቻልም ባንኮቹ ከወዲሁ ሊያጤኑት ይገባል:: በተጨማሪም ሌሎች ባንኮችን ሄደው መጎብኘት አለባቸው" ሲሉም አስተያየታቸውን ሰጥተዋል::

በተለይም የቦርዱ አመራርና አሰራር፣ ማኔጅመንቱ የሚያስተዳድርበትን መንገድና ሥርዓት፣ የህግ ማዕቀፎች፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምና የሰው ኃይል አስተዳደር ጭምር ማወቅ ተገቢ መሆኑን አሳስበዋል::

ወደዚህ ሥራ ለመግባትም የፋይናንስ ተቋማት ካፒታላቸውን ማሳደግ እንዳለባቸው የገለፁት ምክትል ገዥው፤ ቀደም ሲል የነደፉትን ስትራቴጂ ብቻ መጠቀም ሳይሆን መልሰው ማየትና መከለስ አለባቸው፤ ከሚመጣው ሁኔታ አኳያ እነዚህንና ሌሎች ሁኔታዎችን ታሳቢ የሚያደርጉ ጉዳዮችን በሙሉ ጥንቃቄ በተሞላው መንገድ መሥራት ይገባል ሲሉም ጠቅሰዋል::

በአጠቃላይ ባንኮች መጪውን ጊዜ እና ቴክኖሎጂ ማዕከል ያደረገ ሥራ እና አቅም መገንባት ብሎም በሴክተሩ ላይ የተሻለ ልምድና እውቀት አካብተው መገኘት እንዳለባቸው አቶ ሠለሞን አሳስበዋል::

# ስፖርት





# መስማት የተሳናቸው ስፖርቶች ፌዴሬሽን በበጀት እጥረት ውድድሮቹን ሰረዘ

**ዓለማየሁ ግዛው**

የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ስፖርቶች ፌዴሬሽን የጠረጴዛ ቴኒስና የእጅ ኳስ ቻምፒዮናን በበጀት እጥረት ማካሄድ እንዳልቻለ አስታወቀ፡፡ ችግሩን ለመቅረፍ ለክልሎች ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ላይ እንደሚሠራም ገልጿል፡፡

በኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ስፖርቶች ፌዴሬሽን የሚዘጋጁ ውድድሮች ዓላማቸው መስማት የተሳናቸውን የኅብረተሰብ ክፍሎች በስፖርቱ በማሳተፍ ተጠቃሚ ለማድረግ ነው፡፡ ከነዚህም ውስጥ የተሻሉ ስፖርተኞችን በመምረጥ በዓለም አቀፍ ውድድሮች አገርን ወክሎ ውጤት ማምጣት እንዲችሉ ማድረግ ነው፡፡ ፌዴሬሽኑ ለ2015 ዓ.ም ሦስት ውድድሮችን ለማካሄድ ያቀደ ቢሆንም የበጀት እጥረት ገጥሞታል። ፌዴሬሽኑ ሊያካሂድ ካቀዳቸው ውድድሮች ማሳካት የቻለውም የአትሌቲክስ ውድድርን ብቻ ነው፡፡

መስማት የተሳናቸው ስፖርቶች ፌዴሬሽን የገጠመውን የገንዘብ እጥረት ለመቅረፍ የድጋፊ አካላት እና የመንግሥት ድጋፍ በበቂ ሁኔታ ባለመኖሩ ውድድር ለመዘጋጀት ተቸግሯል። ይህም ብዙ ውድድሮች እንዲሰረዙ አድርጓል፡፡ በዚህም ምክንያት መስማት የተሳናቸው ስፖርተኞች ስፖርት ውስጥ የመሳተፍ ዕድላቸው አነስተኛ እንዲሆን አድርጓል፡፡

ፌዴሬሽኑ የጠረጴዛ ቴኒስ እና የእጅ ኳስ ቻምፒዮናን ለማካሄድ አዘጋጅ ክልል መርጦና የውድድር ቀን ቆርጦ



**አቶ ኃይለማርያም ታረቀኝ፣**

የነበረ ሲሆን ክልሎች በበጀት እጥረት ምክንያት መሳተፍ እንደማይችሉ መግለጻቸውን አሳውቋል፡፡ የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ስፖርቶች ፌዴሬሽን ከእጅ ኳስ ፌዴሬሽንና ከጠረጴዛ ቴኒስ ፌዴሬሽን ጋር ውድድሮቹን ለማዘጋጀት ዝግጅቱን ቢጨርስም ክልሎች አለመሳተፋቸውን ተከትሎ ውድድሮቹን ለመሰረዝ ተገዷል።

ውድድሩን ለማስተናገድ ድሬዳዋ ከተማ በዝግጅት ላይ የነበረ ቢሆንም በዚሁ ምክንያት ሊሰረዝ ችሏል፡፡ ለዚህም ፌዴሬሽኑ በደብዳቤ ለሚመለከታቸው አካላት ማስታወቁን ገልጿል፡፡

የስፖርት ኢንዱስትሪ ውስጥ መስማት ለተሳናቸው ስፖርተኞች ተገቢው ትኩረት እንዳልተሰጠ የተጠቆመ ሲሆን፣ ከፋይናንስ እጥረት ባሻገር በዚህ ስፖርት ዘርፍ በቂ ግንዛቤና ዕውቅና አለመኖሩ ምክንያት ተደርጓል። መስማት የተሳናቸው ስፖርተኞች እራሳቸውን የሚያሳዩበት ይህ መድረክ ልዩ ትኩረትና ድጋፍ ከሚሹ ዘርፎች መካከል አንዱና ዋነኛው መሆኑም ተጠቁሟል።

በዚህም መስማት የተሳናቸው ስፖርተኞች በቂ ትኩረትና ድጋፍ እንዲያገኙ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ለመሥራት ጥረት እያደረገ እንደሚገኝ ፌዴሬሽኑ አስታውቋል፡፡ ወደ ክልሎች ወርዶ የክትትልና ድጋፍ ሥራዎች በስፋት መሥራትም ታስቧል። በተጨማሪም ፌዴሬሽኑ ከኦሊምፒክ ኮሚቴና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ጥምረት ፈጥሮ መሥራትን እንደ አማራጭ ይዟል፡፡ እያንዳንዱን የውድድር ዓይነት ከየፌዴሬሽኑ ጋር አስተሳስሮ እገዛ እንዲያደርጉ በማድረግ የስፖርተኞቹን ተሳትፎና ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ለማድረግም እንደሚሠራ ገልጿል።

የኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ስፖርቶች ፌዴሬሽን ባለሙያ አቶ ኃይለማርያም ታረቀኝ በኅዳር ወር በተካሄደው ጠቅላላ ጉባኤ ውድድሮችን ጥርና የካቲት ለማድረግ ቢታቀድም የበጀት ድጎማው በወቅቱ ባለመለቀቁ ውድድሮቹ እየተሸጋሸጉ መምጣታቸውን ተናግረዋል፡፡ የበጀት ድጎማው ሲለቀቅ ፌዴሬሽኑ ውድድሮችን ለማዘጋጀት ለክልሎች ቢያሳውቅም ክልሎች በጀታቸው እያለቀ በመምጣቱ እጥረት ሊያጋጥማቸው ችሏል፡፡ በዚህም ምክንያት በውድድሩ መሳተፍ እንደማይችሉ ማሳወቃቸውን ባለሙያው አስረድተዋል። «በቀጣይ ሁለት ወራት ክልሎች ጋር ወርደን ክትትልና ድጋፍ አድርገን ለምን በጀት እንደልተመደበና ትኩረት አልተሰጠውም የሚለው ጉዳይ ላይ ከክልሎች ጋር መግባባት ለመፍጠር ይሠራል» ያሉት ባለሙያው፣ ፌዴሬሽኑ ስለ መስማት የተሳናቸው ስፖርቶች አስፈላጊነት እና የተሳትፎ ፋይዳ ለክልሎች ግንዛቤ መፍጠር ላይ ትኩረት ሰጥቶ ለመሥራት እቅድ መያዙን አብራርተዋል። ይህም ተሳትፎውን ለማሳደግና ለማነቃቃት ይረዳል ተብሎ ታምኖበታል። ግንዛቤን ከመፍጠር በተጨማሪ መስማት ለተሳናቸው ስፖርተኞች የተሳትፎ እድገት ኢንቨስት ማድረግ የሚፈልጉ ተጨማሪ ድጋፍ ሰጪዎችን ለመሳብ ይረዳል ተብሎም ይጠበቃል።

ፌዴሬሽኑ ስፖርቱ መስማት ለተሳናቸው ስፖርተኞች ብቻ አለመሆኑን በመጠቆም በዚህ ረገድ ያለውን የተዛባ አመለካከት ለመለወጥ ጥረት እያደረገ ይገኛል። መስማት የተሳናቸው ስፖርተኞች ልክ እንደማንኛውም ሰው ያሰቡትን ሁሉ ማሳካት እንደሚችሉ ለሌላው ማኅበረሰብ ለማሳየት ቁርጠኛ መሆኑንም ገልጿል።